Happy Birth Day Happy Birth Day Happy Birth Day

ዘንድሮም የልጅዎን ልደት
በኬክ፣ በለስላሳ፣ በከረሜላና ከአንድ ቀን
በላይ ዕድሜ በሌላቸው ውድ ነገሮች ነው
የሚያከብሩት?

# ወይስ

በቁም ነገር መፅሔት ላይ የዕድሜ ልክ
ዶክመንት ያኖሩላቸዋል?

ቦታ ለመያዝ ፈጥነው ይደውሉ!

ለልጅዎ ምኞትዎን ይግለፁ!

ታሪክን ያኑሩ!

# ደብዳቤዎቻችሁ

## "የአባቶቻቸው ልጆች!"

ሰላም ውድ ቁምነገሮች፤ እንዴት ናችሁ?

ባለፈው ሳምንት የተከበረው የዓድዋ ድል በዓል ላይ በዳግማዊ ምንሊክ አደባባይ ተገኝቼ ነበር፡፡ በጣም ደስ የሚል ነበር አከባበሩ፡፡ በተለይ ካለፈው ዓመት ጀምሮ የእቴጌ ጣይቱና የአፄ ምንሊክን ምስሎች በቲሸርቶቻቸው አሠርተው በቡድን በመኾን ትርኢት የሚያቀርቡ ወጣቶች ቁጥር እየጨመረ መምጣቱ አስደሳች ነው፡፡ እነኚህ የአባቶቻቸው ልጆች በፈጠሩት ልዩ ድምቀት ሚዲያዎቻችንም ላይ መነቃቃት ዓይቻለሁ፡፡ በርቱልኝ በሉልኝ፡፡

ሳሙኤል ዳኘው - ከአዲስ አበባ

## ‹‹ነፍስ ይማር!››

ውድ የቁም ነገር መጽሔት አዘጋጆች፤ እንዴት ናችሁ

ዕውቁ የኪነጥበብ ሰው ጌታቸው ደባልቄ ባለፈው ሳምንት ከዚህ ዓለም በሞት መለየታቸውን በመስማቴ እጅግ አዝኛለሁ፡፡ ‹ምነው ተለየሽኝ› እና ‹አደረች አራዳ›ን የመሳሰሉ ዘመን መሻገር የሚችሉ ድንቅ ሙዚቃዎች የደረሱ የጥበብ አባት መሞታቸውን መስማት ያሳዝናል፡፡ እንደርሳቸው ዓይነት በቴአትሩም፣ በሙዚቃ ድርሰቱም የተሳካለት ዕንቁ ባለሙያ ማግኘት ዕድለኝነት ብቻ ሳይሆን ከፍተኛ ጥረት የሚጠይቅ በመሆኑ የዘመኑ አርቲስቶች ከጋሽ ጌታቸው ብዙ ሊማሩ ይገባል፡፡ ነፍስ ይማር!

ትዝታ ሰለሞን - ከድሬዳዋ

## ‹‹ይክበሩልን!››

ይድረስ ለቁም ነገር አዘጋጆች!

የጉዞ አድዋ ስድስት ተሳታፊዎች ዘንድሮ ለመጀመርያ ጊዜ የካራማራ ጀግኖችን ማሰባቸው እጅግ የሚያኮራ ነው፡፡ ድሉን ለመዘከርም አዲስ አበባ በሚገኘው ‹ድላችን› ሐውልት ስር አበባ ማስቀመጣቸውን በፌስ ቡክ ተመልክቻለሁ፡፡ ይህ የተረሱ ጀግኖችን የማሰብ በጎ ተግባር በሌሎችም ወጣቶች አርአያነቱ ሊወሰድ ይገባል፡፡ የጉዞ አድዋ ስድስት ተሳታፊዎች ግን ክበሩልኝ ብያለሁ፡፡

ሙሉዓለም ስለሺ - ከአዲስ አበባ

# ማውጫ

5

ምናልባት የኢህአዴግን መቃብር ለማዘግየት አልያም ለማስቀም የሚሞከር እርምጃ በእነ ህሰወሃት በኩል እየተደረገ ስለመሆኑ የተረጋገጡ መረጃዎች ባይኖርም ራስን ከሚመሰረተው አዲስ ሀገር አቀፍ ፓርቲ የማግለል እርምጃ እንደ ዋነኛ አማራጭ ሲኖር እንደሚችል ግን ይገመታል፡፡

7

ስለ አድዋ ለማስጠናት የግድ አዲስ ዩኒቨርሲቲ መገንባት አለበት ያለው ማነው አልክ? ለምን በአሁን በስራ ላይ ካሉት 44 ዩኒቨርሲቲዎች መሀከል አንዱን ለፓን አፍሪካ ዩኒቨርሲቲ ሰጥቶ ወይም ስለ አድዋ የሚያስተምር ትምህርት ክፍል ከፍቶ የተበጀተውን በጀት ለሌላ የልማት ስራ አይውልም አልክ? ምናልባት ይሄ ይሆናል የጠቅላይ ሚኒስትሩ ምላሽ፤

9

በግብታዊነት በሚሰጥ ሀላፊነት በተወሰኑ ጥቂት ግለሰቦች አማካሪነት የሚካሄድ ሳይሆን የሀገሪቱን ታሪካዊና ተጨባጭ የሰብአዊ መብት ጥሰቶችና የተወሳሰቡ ችግሮች (ቅራኔዎች) በጥንቃቄ ባገናዘበ ሁኔታ የተለያዩ ባለድርሻዎችን ያሳተፈ አስመራጭ ኮሚቴ በኮሚሽን አባላቱ ምርጫ ላይ ሀላፊነት ወስዶ በቀጥታ ሲመራው ይገባል፤


18

**አልጃዚራ ቴሌቪዥን በጎርጎሪዮሳዊው 2017 ጥቅምት ወር ዘገባው ለወትሮ ቡና ታስተናግድ የነበረችው የየመኗ ሞካ ወደብ በሳውዲ መራሹ ጥምር ኃይል ቁጥጥር ሥር መቆየቷን አመልክቷል።**


<u>የሚቀጥለው ዕትም</u>

ቁም ነገር መፅሔት ቁጥር 380 ዕትም

መጋቢት 7 ቀን 2011 ዓ.ም ይጠብቋት!



4



14



24

# ከአዘጋጁ





## ተከብረሽ የኖርሽው ባባቶቻችን ደም እናት ኢትዮጵያ የደፈረሽ ይውደም

ማህሙድ አህመድ

ከጥቂት ዓመታት በፊት የተጀመረው የበጎ ሰው ሽልማት በየዓመቱ የሚካሄድ ፕሮግራም ነው፡፡ በአንድ ወቅት ከሽልማት ሥነ ሥርዓቱ ቀደም ብሎ ስለዝግጅቱ በተጠራ ጋዜጣዊ መግለጫ ላይ ለፕሮግራሙ አዘጋጆች ከጋዜጠኞች የቀረበ አንድ ጥያቄ ነበር፡፡ ‹ የበጎ ሰው ሽልማት ከሚሸልማቸው ዘርፎች መሀከል የዓመቱ የሰላም ሰው የሚል ነበር፡፡ ነገር ግን ዘንድሮ የለም፤ ለምንድነው?› የሚል፡፡ ከፕሮግራሙ አዘጋጆች መሀከል አንዱ የሆነው ዲያቆን ዳንኤል ክብረት « ለዘንድሮ ብቻ ሳይሆን ላለፉት ተከታታይ ዓመታት የዓመቱን የሰላም ሰው፤ ለመሸለም ዝርዝራችን ውስጥ ነበር፡፡ ነገር ግን የሰላም ሰው ብለን የምንሸልመው መስፈርቱን የሚያሟላ ሰው ባለማግኘታችን ልንሸልም አልቻልንም፡፡» ሀገሪቷ ካሏት 90 ሚሊየን ህዝብ ውስጥ ለተከታታይ ዓመታት አንድም የሰላም ሰው መፍጠር አለመቻላችን ማህበረሰባችን ህመም ላይ መሆኑን አመላካች ይመስላል፡፡

ያስፈራል! በእርግጥ ያስፈራል! ለዘመናት ተዋዶና ተከባብሮ ይኖር የነበረ ህብረተሰብ በድንገት ለፍጅት ሲጠራራ ማየት ያስደነግጣል፡፡ በሀይማኖታችንም ሆነ በባህላች ያልታየ፤ ያልተሰማና፤ ፈፅሞ ይሆናል ብሎ ለመገመት የሚያስቸግሩ ነገሮች ከጥቂት ወራት ወዲህ በሀገራች ክልሎች እዚህም እዚያም እያየን ነው፡፡

በትግራይና በአማራ ክልሎች በተፈጠሩ አለመግባባቶች የሰው ህይወት ከመጥፋት ከጀመረ ውሎ አድሯል፡፡ህግን ለማስከበር ሀላፊነት ባለበት የፀጥታ ሀይልም ሆነ በህብረተሰቡ መሀከል የተፈጠረው አለመግባባት መተኪያ የሌለው የሰው ልጅ ህይወትን ቀጥፏል፡፡

የዚህ አይነት ችግር በሀገሪቱ ሲከሰት የአስታራቂነት ሚናቸውን መወጣት የነበረባቸው አካላት በራቸውን ዘግተው ሁኔታውን እያዩና እየሰሙ ዝም ማለታቸው አሳሳቢ ነው፡፡ ማንም ሰው የማይሞትባት ወይም የማይገደልባት ኢትዮጵያን መገንባት የሁላችንን ሀላፊነት ነው፡፡ በተለይም የሀይማኖት አባቶችና ምሑራን፤እንዲሁም የኪነጥብብ ባለሙያዎችና የመገናኛ ብዙሃን ባለሙያዎች ከፍ ያለ ሀላፊነታቸውን ሊወጡ የሚገባበት ሰዓት ላይ እንገኛለን፡፡

በቅርቡ በመንግስት ተመሠረተው የሰላምና የእርቅ ኮሚሽንም ገለልተኛና በጉዳዩ ላይ ተጠያቂ ሊሆኑ የሚገባቸውን ሰዎች ከማካተቱ አንፃር የተአማኒት ችግሩን በአፋጣን ፈትቶ ወደ ስራ ሊገባ ይገባል እንላለን፡፡፡

**እግዚአብሔር ኢትዮጵያንና ሕዝቦቿን ይባርክ!**






**ለቁም ነገር እንሠራለን!**

**በቁም ነገር ሚዲያና ኢንተርቴመንት ኃ/የተ/የግ/ማ ሥር እየታተመ በየሳምንቱ የሚወጣ በኪነ ጥበብና በማህበራዊ ጉዳዮች ሳይ የሚያተኩር መፅሔት**

በ1994 ዓ.ም ተመሰረተ

17ኛ ዓመት ቁጥር 379

ዋና አዘጋጅ፡- ታምራት ኃይሉ / 0911 23 20 15

የካ ክ/ከተማ ቀበሌ 13/14 የቤት ቁጥር 212

ም/ዋና አዘጋጅ፡-ፍስሀ ጌትነት/fishmarti09@gmail.com

ሪፖርተር፡- ማዕረጉ ተስፋሁን

ዘካሪያስ ተክሌ

አማካሪ፡- ካሣ ለገሠ (ከ አሜሪካ ቨርጂኒያ)

ግራፊክስ ዲዛይነር፡- ተክለ ኪዳነ አምባዬ

ኮምፒውተር ፅሁፍ፡- ማህሌት ካህሳይ

ሽያጭና ስርጭት፡- ቴዎድሮስ ንጉሴ /0913-887175/

ሕትመት ክትትል፡- በዛብህ ተክሉ/0911-416800/

የዝግጅት ክፍሉ አድራሻ

ቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 04 የቤ.ቁ 43/02/03

ቅዱስ ኡራኤል ቤተክርስቲያን ህንጻ 5ኛ ፎቅ

ቢሮ ቁጥር 43/02/03

ስልክ፡- 011-5-507410 / ፋክስ፡-011-5-507410

ፖስታ፡- 25099 ኮድ 1000 አ.አ

ኢሜይል፡- kumneger10@gmail.com

አታሚ ቢኒያምና በቀለ የህትመት አገልግሎት

አድራሻ፡- የካ ክ/ከተማ ወረዳ 07 የቤት ቁጥር 363

ስልክ 0922446324

# በመጨረሻም .... ወደ መቃብር



# ‹ኢህአዴግ› ከ1981- 2011



‹ኢህአዴግ አብረን እንሁን ብሎ ማንንም አያስገድድም ›

‹‹ሰማዕታ የወደቁለትን ዓላማ ሳናሳካ ድርጅቱን አናፈርስም›

ኢህዴዴግ የሚባለው ግንባር የተመሰረተው በ1981 ዓ.ም አጋማሽ ሲሆን የግንባሩ ዋነኛ ተዋንያን ህወሃትና የቀድሞው ኢህዴን/ብአዴን ነበሩ፡፡ በዓመቱ የተማረኩ ወታደሮችና ሌሎች ተራማጅ የኦሮሞ ወጣቶችን ያሰባሰበው ኦህዴድን በመመስረት የግንባሩ አካል ማድረጉ ይታወሳል፤



መነሻ

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር ዐብይ አህመድ የኢህአዴግ አባልና አጋር ድርጅቶች ከጥቂት ወራት በኋላ አንድ ሀገራዊ ፓርቲ እንደሚመሠርቱ አስታውቀዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በቅርቡ ከ3 ሺህ በላይ ከሚሆኑ ከሐረሪ፣ ጋምቤላ፣ ቤኔሻንጉል ጉሙዝ፣ ከአፋርና ከሶማሌ ክልል ከተውጣጡ የማኅበረሰብ ተወካዮች፣ የሃይማኖት መሪዎችና የሀገር ሽማግሌዎች ጋር በጽሕፈት ቤታቸው በሀገራዊ ለውጡ መሠረታውያንና አካሄድ ዙሪያ ምክክር ሲያደርጉ ከዋሉ በኋላ ነው ይህንን ያሳወቁት፡፡ «ከጥቂት ወራት በኋላ የአፋር፣ የቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ የሶማሌ፣ የኦሮሞ፣ የአማራ … ፓርቲ እያልን አንሄድም። እንደ ኢህአዴግ ከጫፍ ጫፍ ያሉ ሁሉም ኢትዮጵያውያን በነፃነት የሚሳተፉበት አንድ ሀገራዊ ፓርቲ እንመሠርታለን» ሲሉ ተደምጠዋል፡፡

ኢህደዴግ የሚባለው ግንባር የተመሰረተው በ1981 ዓ.ም አጋማሽ ሲሆን የግንባሩ ዋነኛ ተዋንያን ህወሃትና የቀድሞው ኢህዴን/ብአዴን ነበሩ፡፡ በዓመቱ የተማረኩ ወታደሮችና ሌሎች ተራማጅ የኦሮሞ ወጣቶችን ያሰባሰበው ኦህዴድን በመመስረት የግንባሩ አካል ማድረጉ ይታወሳል፡፡ በ1985 ዓ.ም ደግሞ የደቡብ ህዝቦችን ለማቀፍ የተመሰረተው ደህዴን የግንባሩ አንድ አባል በመሆን ወደ ምርጫ ጉዞ ጀምሯል፡፡

ለኢህአዴግ ምስረታ የአንበሳውን ድርሻ የያዘው ህወሃት የሰሞኑ የጠቅላይ ሚኒስትሩ መግለጫ ያስደሰተው አይመስልም፡ ፡ ምንም እንኳ አጋር ፓርቲዎችን የማቀፍና በኢህአዴግ ውስጥ የማስገባት ፍላጎትና ጥያቄ በየጊዜው ሲነሳ የቆየ ጉዳይ ቢሆንም በዚህ ቀውጢ ሰዓት ኢህአዴግን ለማፍረስና በአዲስ ፓርቲ ለመተካት የተያዘውን ሩጫ ህወሃት በጥርጣሬ እየተመለከተው ነው፡፡ ከጥቂት ሳምንታት በፊት ገዢው ፓርቲ ኦዴፒ በአንድነት ሀይሎች ዓላማው ተጠልፏል በሚል ለተጀመረበት ዘመቻ ምላሽ በሚመስል ሁኔታ ‹በፌደራሊዝም ስርዓቱ ላይ ድርድር የለም› የሚል መግለጫ ቢያወጣም ህወሃት አሁንም ልቡ ከኦዴፒ ጋር ለማድረግ መቸገሩን የፖለቲካ ሳይንስ ሙሑራን ይመሰክራሉ፤

በመሆኑም ህወሃት በጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር አብይ አህመድ የተነገረውን ኢህአዴግን የማፍረስ እርምጃ ለመቀበል እያንገራገረ መሆኑ ይታያል፡፡ ህወሃት ብቻ ሳይሆን የብሔር ፌደራሊዝሙ የህልውናችን መሠረት ነው ብለው እንደ ህወሃት የሚያምኑ የአፋር፣ የቤንሻ ጉል ጉምዝና የጋምቤላ ፓርቲዎችም የህወሃትን መንገድ ለመከተል እንደሚፈልጉ ከድርጅቶቹ መሪዎች መግለጫ መረዳት ይቻላል፤

ያም ሆኖ ግን ይህ ኢህአዴግን ወደ አንድ ሀገራዊ ፖርቲ የማምጣት ውሳኔ በህዋሳው የኢህአዴግ ውሳኔ ላይ የተነሳ ከመሆኑ ጋር በተያያዘ ህወሃትም ሆኑ ሌሎች አጋር ፖርቲዎች ኢህአዴግን እያለቀሱ ወደ መቃብር ከመሸኘት በቀር አማራጭ ያላቸው አይመስልም፡፡ ምናልባት የኢህአዴግን መቃብር ለማዘግየት አልያም ለማስቀም የሚሞከር እርምጃ በእነ ህሰወሃት በኩል እየተደረገ ስለመሆኑ የተረጋገጡ መረጃዎች ባይኖርም ራስን ከሚመሰረተው አዲስ ሀገር አቀፍ ፓርቲ የማግለል እርምጃ እንደ ዋነኛ አማራጭ ሊኖር እንደሚችል ግን ይገመታል፡፡

ለዚህም ይመስላል በጠቅላይ ሚኒስትር አብይና በኦዴፒ በኩል የሀገራዊው ፖርቲ አባል ለመሆን የማይፈልግ ድርጅት ካለ ‹መንዱን ጨርቅ ያርግለት› አይነት የቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ መለስ ዜናዊን ንግግር የሚያስታውስ ምላሽ ያስነገረው፡፡

“

**ምናልባት የኢህአዴግን መቃብር ለማዘግየት አልያም ለማስቀም የሚሞከር እርምጃ በእነ ህሰወሃት በኩል እየተደረገ ስለመሆኑ የተረጋገጡ መረጃዎች ባይኖርም ራስን ከሚመሰረተው አዲስ ሀገር አቀፍ ፓርቲ የማግለል እርምጃ እንደ ዋነኛ አማራጭ ሊኖር እንደሚችል ግን ይገመታል፡ ፡ ለዚህም ይመስላል በጠቅላይ ሚኒስትር አብይ የሀገራዊው ፓርቲ አባል ለመሆን የማይፈልግ ድርጅት ካለ ‹መንዱን ጨርቅ ያርግለት› አይነት የቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ መለስ ዜናዊን ንግግር የሚያስታውስ ምላሽ ያስነገረው፡፡**

ለዚህ ደግሞ እንደ እንደ ማስረጃ የሚጠቀሰው የኢህአዴግ ጽሕፈት ቤት ምክትል ኃላፊ አቶ መለሰ አለሙ፤ ለአዲስ ዘመን ሰሞኑን በሰጡት ማብራሪያ ‹በዓላማ የሚጣጣም ካለና ዓላማውን የሚደግፍ ፓርቲም ሆነ ግለሰብ አብሮ ለመስራት ከፈለገ የኢህአዴግ በር ክፍት መሆኑን ገልጸው፤ ግን አብረን እንሁን ብሎ ማንንም አያስገድድም ብለዋል። ኢህአዴግ የህዝብ ድርጅት ነው ያሉት አቶ መለሰ፤ በባህሪይው ተራማጅ በመሆኑ እንደየጊዜው ስልቶቹን በመንደፍ አገሪቱን ከኋላ ቀርነት በማውጣትና የዳበረ ዴሞክራሲ በመፍጠር የበለጸገች ኢትዮጵያ ለመገንባት ይሰራል።› ማለታቸውን የዙሩን ክረት ያሳያል፡፡

በመሆኑም ኢህአዴግ የመፍረሱና ወደ መቃብር የመውረዱ ጉዳይ የማይቀር ቢሆንም የኢህአዴግን ግብር ይዘው የሚቀጥሉ እንደ ህወሃት አይነት ድርጅቶች በዚያው መንገድ የርዕዮተ ዓለም ለውጥ ሳያደርጉ የሚቀጥሉበት እድል ዝግ አለመሆኑን ማየት ይቻላል፡፡ ህወሃት ለድርጅት ካድሬዎቹና ለአባላቱ እንደተናገረው ‹ሰማዕታ የወደቁለትን ዓላማ ሳናሳካ ድርጅቱን አናፈርስም› የሚል ይዘት ያለው መልዕክት ማስተላለፉ ተሰምቷል፡፡ ይህም ህወሃት ከኢህአዴግ ውህድ አዲስ ፖርቲ ጋር ላለመጓዝ ፍላጎት እንዳለው ማሳያ ነው፡፡ ህወሃት በዚህ ጊዜ የኢህአዴግን መፍረስ ብቻ ሳይሆን ቀደም ሲል በተቃዋሚነት ጎራ ውስጥ የተሰለፉ እንደነ አቶ ሌንጮ ለታ አይነት ድርጅት አስቀድሞ ከኦዴፒ ጋር የመዋሃዳቸው ጉዳይ የመስመር ልዩነቱን ግልፅ ሳያደርገዋል አልቀረም የሚሉ ወገኖች አሉ፡፡ ይም ሆኖ ግን የኢህአዴግ መፍረስና የአዲስ ፖርቲ መመስረት በምን መልኩ ይሆናል የሚለው ውሰብስብ ጥያቄ መቼና እንዴት እንደሚፈታ ለመገመት ሁኔታዎች አስቸጋሪ ናቸው፡፡

ኢህአዴግ የቅርፅ ብቻ ሳይሆን የስም ለውጥም እንደሚያካሂድ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ተናገረዋል፡፡ ይህም ባለፉት 27 ዓመታት በሀገሪቱ ከተፈፀሙት የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችና ሰቆቃዎች ጋር ተያይዞ ስሙ ምቾት ለማይሰጣቸው ወገኖች እፎይታ መስጫ ተደርጎ ተወስዷል፡፡

## ኢህአዴግ ወደ መቃብር መቼ?

በጥቂት ጊዜ ውስጥ የጥናቱ ውጤት ተጠናቅቆ የኢህአዴግ አባል ድርጅቶችና አጋር ድርጅቶች መክረው የጋራ ካደረጉት በኋላ አንድ ሀገራዊ ፓርቲ የሚመሠርቱ መሆናቸውን የገለጹት ዶ/ር አብይ ኢህአዴግ በሐዋሳው ጉባዔ ባሳለፈው ውሳኔ መሠረት አጋር ድርጅቶችን ወደ ግንባሩ ለማስገባት ጥናት እንዲካሄድ መወሰኑን አስታውሰዋል።

“በሀገሪቱ የመጣው ለውጥ በመላ ኢትዮጵያዊ ጥረትና መስዋዕትነት መሆኑ ተረድተን ካላከበርነው ልክ በፍጥነት እጃችን እንደገባው በፍጥነት ከእጃችን ሊወጣ ይችላል። ስለዚህም ያገኘናቸውን ድሎችና ውጤቶች በትክክል እያከበርን የቀረውን ለመሙላት መጓዝ ያስፈልጋል” ያሉት ዶ/ር አብይ “የመንግሥትን የለውጥ እንቅስቃሴ መደገፍ እንዲችሉ የተቋማትን አቅም መገንባት አስፈላጊ ነው። ከዚህም በተጨማሪ የዴሞክራሲ ሥርዓቱን ለማዳበር የሕዝቦች ፈጣንና ወትሮ ዝግጁነት ያለው ተሳትፎ አስፈላጊ ነው። የምንፈልጋትን ኢትዮጵያ ለማየት የሁላችንንም ተሳትፎ ይፈልጋል” ሲሉም ተናግረዋል።

“አንድ ኢትዮጵያዊ ፓርቲ ሁላችንም ያለንበት በመፍጠር ሁሉም ኢትዮጵያ እኩል የሚነጋገርበት እኩል የሚወስንበት ድምጹ የሚሰማበት ከየትኛውም ጫፍ ብቃት ያለው ሰው በየትኛውም ኃላፊነት ክለከላ የማይደረግበት ስርዓት ለመፍጠር ለውጡ በፍጥነት እየተጓዘ ይገኛል” ያሉት ዶ/ር አብይ ከአጋር ድርጅቶችና የማኅበረሰብ አባላት ለቀረቡላቸው የተለያዩ ጥያቄዎችም ምላሽ ሲሰጡም “ችግሮች የሌሎች ክልል ናቸው ከማለት ይልቅ ኃላፊነትን በመውሰድ የትብብርና መፍትሔ ፈላጊ ባሕልን ማስፈንና በየክልሉ የነዋሪዎችን ቅሬታ መስማት የመሪዎች ተግባር መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል። የህግ የበላይነትን በተመለከተም የሕግ የበላይነት የሚሰፍነው ሕዝቦች ለሰላም ዋጋ ሲሰጡና ሲንከባከቡት እንጂ በጠመንጃ እንደማይመጣ መረዳት መገንዘብ ያስፈልጋል። የመንግሥት ምጣኔ ሀብታዊ የለውጥ እንቅስቃሴ ሥራ አጥነትን ለመቅረፍ፣ የመስኖ ፕሮጀክቶችን በማሳደግ ዘርፍ በቅድሚያ የሚከወን ይሆናል” ብለዋል።

## ቀዳሚው ቃል

በኢትዮጵያ የፖለቲካ ቀውሱን ለመፍታት እና የፖለቲካ ምህዳሩን ለማስፋት መንግሥት ውስጣዊ ችግሮቹን ፈትቶ ሕገ መንግሥቱ በሚፈቅደው መሠረት የመድብለ ፓርቲ ሥርዓትን ማጠናከር እንደሚገባ ምሁራን ያስጠነቅቃሉ፡፡ ገዥው ፓርቲ ኢህአዲግ ከብሄራዊ ድርጅቶች ግንባርነት ወደ ተዋሃደ አንድ ፓርቲ ለመሸጋገር የያዘው ዕቅድ

ወደ ገጽ 22 ዞሯል


# ወጣቱ አማካሪ እና እጣ ፋንታ አንባቢ ዙሮሜል



ወጣቱ አማካሪ ዙሮሜል እጅግ ጥልቀት ያለው የፓልሚስትሪ፣ ኑሞሮሎጂ፤ አስትሮሎጂ፤ የካርታ ንባብና፤ የሳይኪክ ጥበብን አሳክቶ የተካነ ብቻም ሳይሆን በሰው ልጆች ውስጥ የተወሳሰቡ ችግሮች አብጠርጥሮ በመረዳት መፍትሄ ይሰጣል፡፡ ባለጉዳዮች ምንም መረጃ ሳይሰጡ ስለ ራሳቸው ወዲያውኑ ትንታኔ መስጠት ይችላል፡፡ በትዳርና ፍቅር እየኖሩ በሀሳብ የማይግባቡ ተጣማሪዎችን የአንደኛቸውን ስም ብቻ በመቀየር የሰመረ ትዳር እንዲሆንላቸው ያግዛል፡፡ የስራ ፊልድዎን የውጪና የትኛውንም የጎዞ ሚስጥርዎንና የንግድ ጥበብ መስመርዎን የጤና ችግሮዎን፤ የተቃራኒ ጾታዎችን ጥምረት፤ ... ልክ የጫማ ቁጥርዎን ለክተው እንደሚለብሱ ሁሉ ልክ ያለው መሆኑን መረዳት ይገባል፡፡ ዕድለኛ የሚያደርገዎ ፈርጦችን በቀለበት፤ በአንገት ሀብል፤ በብራስሌት፤ ወይም በየትኛውም ቢጠቀሙ ስኬታማ እንደሚደርግዎ ይጠቁሞታል፡፡ ለወሲብ ችግርና ለደም ግፊት መፍትሔ ያገኛሉ፡፡ በተለይ ይህ ስር የሰደደ የፓልሚስትሪ ጥበብ እጅግ የመጠቀ ከመምጣትም አልፎ እስካሁን ለዓለም ህዝብ ያልተደረሰባቸውን ሌላ ከሰባቱ ዝርያዎች ውጪ አምስት ያህል በማግኘት ጥበቡን የበለጠ ከፍ አድርጎታል፡፡ በመሆኑም አዲሱን የጥበብ መጽሐፍ በማዘጋጀት ላይ ይገኛል፡፡

በፖስታ መጠቀም ለምትፈልጉ ደንበኞች 150.00 /አንድ መቶ ሃምሳ ብር/ የከፈላችሁበትን ደረሰኝ ጨምራችሁ በመላክ መጠቀም ትችላላችሁ፡፡ የባንክ ሒሳብ ቁጥር 1000130318014 /ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ/

ለየትኛውም የማማከርና መፍትሔ ለሚፈልጉለት ጉዳይዎ ዙሮሜልን በግንባር ቀርበው ማናገር ይቻላል፡፡
ለማንኛውም አይነት መረጃ 0911-74 91 95/ 0912-80 64 84/ 0118-40 25 51 ፓ.ሳ.ቁ 669/1230 አ.አበባ



# ይልቅ ወሬ ልንገርህ



## ስለ አድዋ ፓን አፍሪካ ዩኒቨርሲቲ ግንባታ የጠቅላይ ሚኒስትሩ ዝምታ

መቼም ሀገሪቷ ዩኒቨርሲቲ በዩኒቨርሲቲ ከሆነች ቆይታለች አይድል? እናስ? እናማ የዛሬ ሁለት ዓመት ገደማ የቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝ የዓድዋን ድል ለመዘከር ለሚገነባው የዓድዋ ፓን አፍሪካ ዩኒቨርሲቲ ግንባታ የሚውል የመሠረት ድንጋይ ጥለው ነበር፤ እናስ? እናማ ስራውን ለማስጀመር ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ጥያቄ ቢቀርብም ምላሹ ዝምታ ብቻ ሆነብኝ ሲል ኮሚቴው እያለቃቀሰ ነው፡፡

እንዴት አልክ? መቼም ጠቅላይ ሚኒስትሩ ‹ከዚህ በኋላ አንድም ግንባታ አናስጀምርም፤ ያሉትን ማስጨረስ እንጂ› ማላታቸውን ታስታውሳለህ አይደል? እናስ፤ እናማ ገንዘብ ለማሰባሰብ የሚያስችል ዝግ የባንክ አካውንት እንዲከፈት ለጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት ጥያቄ አቅርቦ ምላሽ በመጠበቅ ላይ መሆኑን የዓድዋ ፓን አፍሪካ ዩኒቨርሲቲ የምስረታ አስተባባሪ ኮሚቴ ያስታወቀ ሲሆን አሁንም የተሰጠ ምላሽ የለም።

የኮሚቴው አስተባባሪ አቶ ቢተው በላይ ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ እንደተናገሩት፣ለዩኒቨርሲቲው ምስረታ በርካታ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ድጋፍ ለመስጠት ፍላጎት አሳይተዋል። ኮሚቴው ድጋፉን ለመቀበል የሚያስችል የገንዘብ ማስገቢያ የባንክ አካውንት እንዲከፈትለት ለጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት ጥያቄ አቅርቦ ምላሽ በመጠበቅ ላይ ይገኛል፡፡

ከመጋቢት 2010 ዓ.ም ጀምሮ እስካሁን ድረስ ለሦስት ጊዜያት ያህል ጥያቄውን ለጽሕፈት ቤቱ ቢያቀርብም እስካሁን ድረስ ምላሽ አላገኘም፡፡ ከዓለም አቀፍ ድርጅቶች የሚገኘውን ድጋፍ ለመቀበል እንዲሁም ሕዝቡ ከድጋፉ ስለሚገኘው ገንዘብ ማወቅና ገንዘቡም ሕጋዊ አሰራርን ተከትሎ ኦዲት መደረግ ስላለበት በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚከፈት ዝግ የባንክ አካውንት እንደሚያስፈልግ ገልፀዋል፡፡

«ባለፈው ዓመት የፌዴራል መንግሥት ለዩኒቨርሲቲው ግንባታ የገባውን የ200 ሚሊዮን ብር ድጋፍ በቅርቡ ይሰጣል የሚል ተስፋ አለን» ያሉት ሰብሳቢው፣ የትግራይ ክልል መንግሥት 250 ሚሊዮን ብር ለመስጠት ቃል መግባቱንና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር 10 ሚሊዮን ብር መስጠቱን ተናግረዋል፡፡ ሌሎች ክልሎችም ድጋፍ እንደሚያደርጉ ቃል ስለመግባታቸው ጠቁመዋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም፣ «በውጭ አገራት የሚገኙ ኢትዮጵያውያንና የሌሎች አገራት ምሁራንን አነጋግረናል፤ የተለያዩ ኮርሶችን ለማስተማርና የገንዘብ ድጋፍ ለማድረግም ዝግጁ እንደሆኑ ገልጸውልናል» ብለዋል፡፡ በ2010 ዓ.ም በአዲስ አበባና በዓድዋ አገር አቀፍና ዓለም አቀፍ ኮንፈረንሶች መካሄዳቸውን አስታውሰው፣ በወቅቱ ከበርካታ አካላት ጋር ግንኙነት መፈጠሩን አስረድተዋል፡፡ ለግንባታው 10 ቢሊዮን ብር ያስፈልገዋል የተባለው የዓድዋ ፓን አፍሪካ ዩኒቨርሲቲ የመሰረት ድንጋይ በሚያዚያ ወር 2009 ዓ.ም በቀድሞው የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝና በኡጋንዳው ፕሬዚዳንት ዩዌሪ ካጉታ ሙሴቬኒ አማካኝነት መቀመጡ ይታወሳል፡፡

እናስ? እናማ ስለ አድዋ ለማስጠናት የግድ አዲስ ዩኒቨርሲቲ መገንባት አለበት ያለው ማነው አልክ? ለምን በአሁን በስራ ላይ ካሉት 44 ዩኒቨርሲቲዎች መሀከል አንዱን ለፖን አፍሪካ ዩኒቨርሲቲ ሰጥቶ ወይም ስለ አድዋ የሚያስተምር ትምህርት ክፍል ከፍቶ የተበጀተውን በጀት ለሌላ የልማት ስራ አይውልም አልክ? ምናልባት ይሄ ይሆናል የጠቅላይ ሚኒስትሩ ምላሽ፤ አንድ ወዳጄ ይህንን ዜና ሲሰማ ምን አለ መሰለህ? ‹ደግሞ 45ኛ ዩኒቨርሲቲ እንገንባ?ግፍ ነው› በል ቻዎ

# ለባለትዳሮች ብቻ



## መሳሳምና ውድ ዋጋው

ገብሬል ሞሪሴይ ለተባሉት የትዳር ጉዳዮች አማካሪ ከአንድ ሰው እንዲህ የሚል ጥያቄ ቀረበላቸው፡፡ «እኔና ባለቤቴ ለአሥር ዓመታት ያህል በትዳር ውስጥ ነን፡፡ እርሷ ቢያንስ በየቀኑ ደህና አድርጌ እንድስማት ትፈልጋለች፡፡ ወሲብ ስንፈፅም እንኳን ካልተሳሳምን ሌላው ነገር የልቧን የሚያደርስላት አይመስላትም፡፡ ይህ ፀባይ በጣም ይገርመኛል፡፡ መች ነው ስሜቷ ቀዝቀዝ የሚለው



እያልኩም አስባለሁ፡፡ በእርግጥ እኔ መሳሙን አልፈልገውም እያልኩ አይደለም፡፡ ነገር ግን ድግግሞሹ ስላሰለቸኝ ምን ማድረግ እንደምችል አላወቅሁም»

ዶክተር ገብርኤል ለጥያቄው መልስ የሰጡት፤ መሳሳም የፍቅር ግንኙነት ከሚገለጽባቸው ነገሮች አንዱ መሆኑን በማስረዳት ነው፡፡ መሳሳም ፍቅረኞች ወይም ባለትዳሮች ፍላጎታቸውን የሚያሳዩበት አንዱ መንገድ ነው፡፡ ይበልጥ መቀራረብን፣ አክብሮትን፣ ለዚያ ሰው ያለንን የርህራሔና አይጠገቤ ስሜት የምንገልጽበትም ነው፡፡ እንደ ዶክተር ገብርኤል ገለጻ፤ መሳሳም ከወንድ ይልቅ በሴቶች ዘንድ ትልቅ ስፍራ ይሰጠዋል፡፡ አንዲት ሴት በአንድ ስሞሽ ብቻ፤ ወንዱ የፍቅር ጓደኛዋ ሆኖ የሚቀጥል መሆንና አለመሆኑን የመለየት አቅም አላት፡፡

በሳይንሳዊ መንገድ ካየነውም መሳሳም ‹ኦክሲቶሲን› የተባሉትን የአእምሮ ኬሚካሎች ለማመንጨት ይረዳል፡፡ እነኚህ ኬሚካሎች በጥንዶች መካከል ጠንካራ ትስስር የመፍጠር አቅም አላቸው፡፡ ሴቶች ከወንዶች በተለየ ለዚህ ኬሚካል ስሱ ሲሆኑ የሚፈጥርባቸው የደስታ ስሜትም ከወንዶች የሚልቅ ነው፡፡

ማይክ እና ካርሊ የተባሉ ባለሙያዎች ደግሞ ‹መሳሳም በትዳርዎ ወሳኝና ማዕከላዊ ስፍራ ላይ መሆንዎን የሚያረጋግጡበት ነው› ይላሉ፡፡ ጥቅሞቹን ሲዘረዝሩም የተረጋጋን ማድረግና ደስተኛ ሆኖ ለመዝለቅ የሚረዳ መሆኑን በቀዳሚነት አስፍረዋል፡፡ በተለያዩ ፈታኝ ሁኔታዎች ውስጥ ለማለፍ ማነቃቂያ ሆኖ ማገልገሉ፣ ፍቅር ግለቱን ጠብቆ እንዲቀጥል ማድረጉ፣ ደህንነትን ማምጣቱና አብረውት ያሉት ሰው በትክክልም እውነተኛ የትዳር አጋርዎ መሆኑን የሚያውቁበት ማረጋገጫ ሰነድ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

ምንጮች፡- bodyandsoul.com እና fulfillingyourvows.com

# የብሄራዊ እርቅ ኮሚሽን አበረታችና አሳሳቢ ገጽታዎች

## የእርቀ ሰላሙ ጅምር ውጤታማነትን ከፍ ለማድረግ ምን ይደረግ?

አክሊሉ ወንድአፈረው
ethioandenet@bell.net

በሀገራችን በኢትዮጵያ ውስጥ የተጀመረው ለውጥ ቁልፍ በሆኑ ጥያቄዎች ላይ ምላሽ እየሰጠ የሚጓዝባቸው ሂደቶች በሰፊው ይስተዋላሉ። የፖለቲከ ምህዳሩን ከማስፋት (ሊበራላይዜሽን ) ወደ ዴሞክራሲያዊ መሰረት መጣል (ዴሞክራታይዜሽን) ለመሸጋጋር የተለያዩ ድንጋጌዎችን ማውጣት አፋኝ ህግጋትን መሻርና ዴሞክራሲአዊ ስርአትን እውን ሊያደርጉ የሚችሉ ተቋማትንም መገንባት አስፈላጊ ነው።

ተቋም ሲባል ዴሞክራሲአዊ ስርአትን አውን ለማድረግ በቅርጽም በይዘትም የሚያግዙ ተቋማትን እንጂ ማንኛውንም ተቋም ማለት አይደለም። ህወሀት ኢህአዴግ ለ27 አመታት እጅግ ዘግናኝ የሆነ ግፍ የፈጸመው፣ አንድነታችንን ያዳከመውና መራራቅ ስር እንዲሰድ ያደረገው በተቋማት ተደግፎ እንደነበር የሚዘነጋ አይደለም።

በዚህ አንጻር በዚህ ጽሁፍ ውስጥ በቅርቡ የታወጀውን የብሄራዊ እርቅና ሰላም ኮሚሽን ምስረታ በተመለከተ የሚታዩትን አበረታች እና አሳሳቢ ገጽታዎች በተወሰነ ደረጃ እዳስሳለሁ ። ይህን ጽሁፍ በማድረግም ጠንካራ ጎኖቹን ይበልጥ ለማጠናከርና ድክመቶችንም በጊዜው ለማረም ግብአት ይሆናል የሚል እምነት አለኝ። ከዚህ በተጨማሪም ለወደፊቱ በሀገራችን ቁልፍ ጉዳዮች ላይ ለሚወሰዱ እርምጃዎች አንዳንድ ትምህርትንም ይሰጣል ብዩ ተስፋ አደርጋለሁ።

*መነሻ*

ሕዝባችን ያሳለፈው ሰቅጣጭና በመብት መጣስ የተሞላ ታሪክ ሁሉንም የህብረተሰባችንን ክፍል እጅግ ጎድቷል። ይህ ተደጋጋሚ የመብት ረገጣ አለመተማመንን ፣ በሀገር አለመመካትን፣ የበላይና የበታች ስሜትን ወዘተ አስፍኗል።በሀገራችን ታሪክም ሆነ በወደፊት አቅጣጫዋ ላይ ከመግባባት ይልቅ ጥልቅ ልዩነት እንዲሰፍን ሆኗል። በነዚህና ተዛማጅ በሆኑ ምክንያቶችም ሀገራችን በፖለቲካ ምስቅልቅልና በጦርነት አዙሪት ከተተበተበች እጅግ ብዙ ጊዜ ሆኗል።

በሀገራችን ውስጥ በመንግስታትና፣ በህዝብ፣ በመንግስታትና በፖለቲካ ድርጅቶች፣ በተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶች መሀላ፣ በያንዳንዱ ፖለቲካ ድርጅት ውስጥ፤ በተለያዩ ማህበረሰቦች መሀል ወዘተ ግጭቶች፣ አለመተማመኖች ወዘተ እንደተከሰቱ፣ እነዚህም ግጭቶች ባግባቡ ሳይፈቱ እስካሁን እደቀጠሉ ይታወቃል።

ይህን የተወሳሰበ ችግርና እጅግ የተጎዳ የወገኖቻችንን ስብራት ለማከምም ሆነ የተወሳሰበውን ብሶትና አለመግባባት ለመቅረፍ ታላቅ ትግስትን የሚጠይቅ በፍትህና እውነት ላይ የተመሰረተ የብሄራዊ እርቅ ሂደትን ተግባራዊ ማድረግ ተገቢ ነው።

ብሄራዊ እውቅ ወይም እርቀ ሰላም ሲባል ቢያንስ ላለፉት አርባና ሀምሳ አመታት የደረሰውን የሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብት ረዘጣ ያስከተለውን በደልና ሰቆቃ በመመመርመር በቂም በቀል መንፈስ ሳይሆን እውነትን መሰረት ያደረገ ፍትህ ተጎጂዎች እንዲያገኙና አስከፊው የታሪካችንም ምእራፍ ተዘግቶ በይቅር ባይነትና በታደሰ መንፈስ የግጭት አዙሪትን የምንሰብርበት አንድንትን መተሳሰብን፣ እኩልነት የምንገነባበት ሂደት እውን ማድረግ ማለት ነው።

በሀገራችን ውስጥ የ እርቅና ሰላም ኮሚሽን የተመሰረተው በ ታህሳስ 16፣ 2011 (ዲሰምበር 25፣ 2018 http://www.ebc.et/web/ebcnews/-/--1947 ) በጸደቀ አዋጅ ሲሆን የኮሚሽኑ አባላት ስም ዝርዝር ለፓርላማው ቀርቦ የጸደቀው ደግሞ በጥር 28፣ 2011 (በ ፌበርዋሪ 5፣ 2019) ነበር https://www.ethiopianreporter.com/article/14706 በጠቅላይ ሚኒስቴር አብይ የሚመሩት መንግስት ይህን ታላቅ ተግባር እውን ለማድረግ የሚያስችል የመጀመሪያውን እርምጃ መውሰዱ የሚያበረታታና የሚያስመሰግነውም ነው። ይህን ስልም የአዋጁ አላማና የሚሸፍናቸው ጉዳዮች ቢያንስ ከላይ የተጠቀሰውን የብሄራዊ እርቅ ያካትታል በሚል እምነት ነው።

ብሄራዊ እርቅ በሀገራችን ተግባራዊ እንዲሆን ለረዥም አመታት ብዙዎች ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ሲታገሉለት የነበረ ሆኖም በዚህም ህወሀት መራሹ ኢህአዴግ እምቢተኛነትና በተወሰኑ በተቃዋሚው ካምፕ የነበሩ ድርጅቶች ተቃውሞ ሳይሳካ የኖረ ጥሪ ነው። አሁን የሚታየው አዲስ ጅምር አበረታችነቱ እንዳለ ሆኖ፤ ውጤታማ እንዲሆን ደግሞ ገና ከመጀመሪያው በጥንቃቄ ሊታዩ የሚገባቸው ጉዳዮች ውስጥ ጥቂቶቹን ከዚህ በታች አቀርባለሁ። ለግንዛቤ እንዲረዳም በተመሳሳይ የብሄራዊ እርቅ ጎዳና የተጓዙ ሀገሮችን ልምድ ምን እንደሚመስል በመጠኑ አሳያለሁ።



## የእርቀ ሰላሙ ኮሚሽን ተመራጮች መመዘኛና ማንነት ገና ከመጀመሪያው ግልጽ የመሆን አስፈላጊነት

የብሄራዊ እርቅን (እርቀ ሰላም) አላማ ታላቅነት ስንመለከት ይህን እውነታ ተግባራዊ ለማድረግ ሀላፊነቱን የሚሸከሙ ሰዎች እነማን ናቸው ምን አይነት መመዘኛ ማሟላት አለባቸው፤ ምን አይነት ልምድ ፣ ማህበራዊ ከበሬታ ፣ እውቀት፣ ወዘተ ሊኖራቸው ይገባል የሚለው እጅግ መሰረታዊ ጥያቄዎች ሆነው እናገኛለን።

ሂደቱ ገና ከመጀመሪያው በተለያዩ ክፍሎች በተለይም በተጎጂ አካሎች ታማኒነትን እንዲያገኝ ለማድረግ ለዚህ ከፍተኛ ሀላፊነት የሚመረጡ ግለሰቦችን መመዘኛዎች በተመለከተ የተለያዩ ባለድርሻዎች ሀሳብ ሊሰጡበትና ሊስማሙበትም ይገባል። ይህ ሂደት የተጎጂ ወገኖችን ፍትህ ማስገኘትና ስብራታቸውንም ማከም ዋና አላማው ስለሆነም ፣ የነርሱን ግብአት ማካተትን ታላቅ ቦታ የሚሰጠው ተግባር ነው።

በቀጣይነት የህዝብን አመኔታን ለማግኘትም ለዚህ ሀላፊነት የሚመረጡ ሰዎች የሚመረጡበትን መሰረታዊ መመዘኛዎች ለህዝብ ግልጽ ማድረግና እያንዳንዱ ተመራጭም የተባሉትን መመዘኛዎች እንደሚያሟላ ማረጋገጥ እምነትን ለማዳበር እጅግ አሰፈላጊ ጉዳይ ነው።

ከዚህም አልፎ የተመራጮች (የኮሚሽን አባላት ) አመራራጥን በተመለከተም ህዝብ በተለያየ መልክ የእጩዎች ጥቆማ እንዲያደርግና ተከታታይ ግብአት እንዲሰጥ የሚያስችል አሰራርን እውን ማድረግ ብሄራዊ እርቅ የኮሚሽኑን ታአማኒነት ይበልጥ የሚያጠናክር ህዝብ ኮሚሽኑን የኔ ነው ብሎ አመኔታን እንዲሰጠው የሚያግዝ እርምጃ ነው።

በደቡብ አፍሪካ ፣ በሴራሊዮን በላይበሪያም ሆነ በቲሞር የተካሄዱት የእርቅ የኮሚሽነሮች ምርጫዎች መመዘኛዎች ከሞላ ጎደል የሚከተሉትን ያካተቱ ሲሆኑ፣ እነዚህ መመዘኛዎች በህዝብ ግብአት የዳበሩና ለህዝብም በጊዜ ግልጽ ተደርገው እንደነበር መግለጥ ተገቢ ነው።

**የእርቅና ሰላም ኮሚሽን አባላት ምርጫ ነጻ መሆንን ፣ ብቃትና ታአማኒነታቸውንም ለማረጋገጥ የኮሚሽኑን አባላት ምርጫ በመንግስት መሪ በብቸኝነት ወይም በግብታዊነት በሚሰጥ ሀላፊነት በተወሰኑ ምርጥ ግለሰቦች አማካሪነት የሚካሄድ ሳይሆን የሀገሪቱን ታሪካዊና ተጨባጭ የሰብአዊ መብት ጥሰቶችና የተወሳሰቡ ችግሮች (ቅራኔዎች) በጥንቃቄ ባገናዘበ ሁኔታ የተለያዩ ባለድርሻዎችን ያሳተፈ አስመራጭ ኮሚቴ በኮሚሽን አባላቱ ምርጫ ላይ ሀላፊነት ወስዶ በቀጥታ ሲመራው እንደሚገባ የተለያዩ ሀገሮች ልምድ አሳይቷል።**

- በህብረተሰቡ ውስጥ ታላቅ ክብርና ታአማኒነት ያተረፉ ፣ በሰብአዊ መብት ጥሰት ውስጥ በፍጹም ያልተሳተፉ (ተሳትፈዋል ተብሎ የማይጠረጠሩ)
- እጅግ የተወሳሰበ ተግባርን ለማካሄድና ረጅም ሰአት ለመስራት ጤንነትና የአእምሮ ብቃት ያላቸው፣
- እጅግ ሰፊ መረጃዎችን በጥልቀት ለማመዛዘን ብቃት ያላቸው፤
- በሀገሪቱ ውስጥ የተካሄዱ የመብት ጥሰቶችና ቅራኔዎችን በተመለከተ በቂ እውቀት
- በእርቅ ተግባር ስራ ከተቻለም በቅራኔ አፈታት በቂ ልመድ ያላቸው
- የተለያዩ ማህበረሰብ ክፍሎችን የሚያንጸባርቁ
- የሰብአዊ መብት ጥሰት የደረሰባቸው ሰዎችን ሁኔታ የሚገነዘብ ሆኖም ራሳቸው የዚህ ጥቃት ቀጥተኛና ከፍተኛ ተጠቂ ያልሆኑ (ትራማታይዝ ያልሆኑ)
- የፖለቲካ ድርጅት ከፍተኛ መሪ ያልሆኑ፤

የዚህ አይነት ግልጽ አካሄድ ተግባራዊ ባልተደረገበት ተመራጮችም (የኮሚሽኑ አባላት)፡ በምን ሁኔታ እንደተመረጡ ባግባቡ በማይታውወቅበት ሁኔታ ኮሚሽኑ ሰፊ ተቀባይነትና ታአማኒነትን እንዲያገኝ ማድረግ እጅግ ከባድ ይሆናል።

## የእርቅና ሰላም ኮሚሽኑ አባላት አመራረጥ ሂደት ተአማኒነት እንዲኖረው የማድረግ አስፈላጊነት


የተለያዩ ሀገሮች ተመክሮ እንደሚያሳየው ይህን ባለብዙ ፈርጅ የተጠራቀመ ችግር እንፈታለን ብሎ የሚነሳ ክፍል የመጀመሪያው ስራ የእርቀ ሰላሙ ሂደት በሁሉም የህብረተሰብ ክፍሎች በተለይም ሰለባ በሆኑ አካሎች ታአማኒነትን እንዲያገኝ ማድረግ ነው። ይህን ለማድረግም ፣ ሽፍጥን አግላይነትን፣ የሌሎችን ጉዳት ዝቅ አድርጎ መመልከትን ፣ የተወሰኑ ክፍሎች የፖለቲካ መሳሪያ ሆኖ መታየትን ማስወገድ የሚቻልበትን አካሄድ በጥንቃቄ መምረጥና መከተል አስፈላጊ ው።

በዚህም መሰረት ገና ከመጀመሪያው ከሰላምና እርቅ ኮሚሽኑ አባላት አመራረጥ ጀምሮ አካሄዱ ግልጽነት ያለው፤ አግባብ ካላቸው ክፍሎች በተለይም የመብት መጣስ ሰለባ ከሆኑ

ወደ ገጽ 16 ዞሯል

መሐመድ ጅዳ ጋራዥ
Mahammed Jeddah Garage
ኤሲ እንሞላለን፤ ሙሉ ሲስተም እንሰራለን!


- የቶዮታና የተለያዩ መኪናዎችን መለዋወጫ እናስመጣለን!
- ማንኛውም ዘመናዊ የኢንጀክሽን መኪናዎች የሞተር ስራና እድሳት
- የኢንጀክሽን ሲስተም ሰርቪስ እናደርጋለን!
- ከገበያ የጠፉ መለዋወጫዎችን በፍጥነት እናስመጣለን!

አድራሻ፡
እንቁላል ፋብሪካ
አለምጸሐይ ድልድይ የኖክ
ነዳጅ ማደያን አለፍ ብሎ
መኪና መሸጫ አጠገብ

ስልክ 251 913 135972
251 924 045308

# ስለ ሳንባ ምች ማወቅ ያለብዎ ነገሮች



የሳንባ ምች(Pneumonia) ብዙ ግዜ የሚጀምረው በባክቴሪያ፣ ቫይረስ ወይም ፈንገስ ምክንያት በሚፈጠር ኢንፌክሽን ነው።

ሳንባዎች በሚታመሙበት ወቅት ሳንባ ውስጥ የሚገኙ አልቪዮሊ ተብለው የሚጠሩ ትናንሽ ከረጢቶች በፈሳሽ ይሞላሉ።የሳንባ ምች በወጣት እድሜ ላይ ባሉ ጤነኛ ሰዎች ላይ ይፈጠራል። ነገር ግን በሽታው በአዛውንቶች፣ በህጻኖች እና የሌላ በሽታ ታካሚዎች ላይ አደገኛ ይሆናል።

## ምልክቶች

የሳንባ ምች የመጀመርያ ምልክቶች ከጉንፋን እና ብርድ ምልክቶች ጋር ይመሳሰላል። ከዛ በኋላ ከባድ ትኩሳት፣ የብርድ ስሜት እና አክታ የተቀላቀለበት ሳል ይቀጥላሉ።

የሚከተሉት ምልክቶች የሳንባ ምች ታካሚዎች ላይ አዘውትረው ይስተዋላሉ:-

ሳል፤በሳል ወቅት የሚወጣ የዛገ ወይም አረንጓዴ ቀለም ያለው አክታ፤ትኩሳት፤ትንፋሽ ማጠር፤የሚያንቀጠቅጥ የብርድ ስሜት፤የደረት ህመም። ወደ ውስጥ በጥልቀት ሲተነፍሱ የሚብስ።

ፈጣን የልብ ምት፤የድካም ስሜት፤ማቅለሽለሽ ስሜት እና ማስመለስ፤ ተቅማጥ፤ላብ፤ራስ ምታት፤የጡንቻ ህመም፤ ማዞር እና ግራ መጋባት፤የቆዳ ቀለም ለውጥ፤የሳንባ ምች ምልክቶች እንደ ምቹ አይነት እና በሌሎች በሽታዎች መኖር ይለያያል።

## ህክምና

ህክምና በምቹ አይነት እና ክብደት ይወሰናል።የባክቴሪያ ምች በአንቲባዮቲክ ይታከማል የቫይረስ ምች እረፍት በመውሰድ እና በቂ ፈሳሽ በመውሰድ ይታከማልየፈንገስ ምች በጸረ-ፈንገስ መድሃኒቶች ይታከማልየሳንባ ምች ምልክቶችን ለማከም ዶክተሮች የተለያዩ መድሃኒቶችን ያዛሉ። ለትኩሳት፣ ለሳል እና ለህመም የሚሆኑ መድሃኒቶች ይታዘዛሉ።

ከዛም አልፎ በቂ እረፍት እና ፈሳሾች መውሰድ ያስፈልጋል። በቂ ፈሳሽ መውሰድ አክታን በማቅጠን በሳል ወቅት በቀላሉ እንዲወጣ ይረዳል።ምልክቶቹ ከተባባሱ ወይም የታካሚው በሽታ መከላከል አቅም ከወረደ ሆስፒታል መተኛት ሊያስፈልግ ይችላል።ሆስፒታል ውስጥ በደም ዝውውር መልክ ፈሳሾች እና አንቲባዮቲክ ለታካሚ ይሰጣሉ። ኦክስጅንም መስጠት የሚያስፈልግበት ግዜ ሊመጣ ይችላል።

## የሳንባ ምች በልጆች ላይ

የብዙ ልጆች የሰውነት በሽታ መከላከል አቅም ከሳንባ ምች ይጠብቃቸዋል። ልጅ በሳንባ ምች ከተጠቃ ብዙ ግዜ መንስኤው የቫይረስ ኢንፌክሽን ነው።

የሚከተሉት ምልክቶች በልጆች አዘውትረው ይታያሉ:-

መተንፈስ መቸገር፤በቂ ምግብ አለመብላት፤ ሳል፤ትኩሳት፤ውሃ መጠማት፤ ልጆች ደረታቸው ላይ የህመም ስሜት፣ ማስመለስ እና ሳል ሊያጋጥማቸው ይችላል።

በቂ እረፍት መውሰድ እና አዘውትሮ ፈሳሽ መጠጣት አስፈላጊ ነው። ዶክተር ለሆድ ህመም መድሃኒት ሊያዝ ይችላል ግን የሳል መድሃኒት ስለማይረዳ አይታዘዝም። ሳንባ ምች የመታቸው ልጆች አካባቢ ሲጃራ ማጨስ በፍጹም አይመከርም።

### መንስኤ

የሳንባ ምች ቀዳሚ መንስኤዎች የባክቴሪያ እና የቫይረስ ኢንፌክሽን ናቸው። በትንፋሽ ወቅት የሳንባ ምች የሚፈጥሩ ጀርሞች አልቪዮሊ የተባሉት የሳንባ ክፍሎች ውስጥ ገብተው ይባዛሉ።

የሳንባ ምች ተላላፊ ነው። በሳል፣ በማስነጠስ እና ተመሳሳይ ቁሶች በመጠቀም ከሰው ሰው ይተላለፋል።

ባክቴሪያ እና ቫይረሶች የሳንባ ከረጢቶችን በፈሳሽ እንዲሞላ በማድረግ የሳንባ ምች እንዲፈጠር ያደርጋሉ። ኢንፌክሽን ሲፈጠር ሰውነታችን ነጭ የደም ሴሎችን በማምረት ኢንፌክሽኑን ለመዋጋት ይሞክራል።

### ተጋላጭነት

የሚከተሉት ሰዎች ለሳንባ ምች በሽታ ይበልጥ ተጋላጮች ናቸው።ከ5 አመት እድሜ በታች እና ከ65 እድሜ በላይ የሆኑ ሰዎችሲጋራ የሚያጨሱ እና በከፍተኛ ደረጃ የሚጠጡ እንደ ሲስቲክ ፊብሮሲስ፣ ሲኦፒዲ፣ አስም ወይም የኩላሊት፣ ልብ እና ጉበት በሽታ አይነት ህመሞች ያለባቸው በኤችአይቪ ወይም ካንሰር ምክንያት የተዳከመ የሰውነት በሽታ መከላከል አቅም ያላቸው ለጀርድ በሽታ መድሃኒት የሚወስዱኩብርድ ወይም ኢንፍሉዌንዛ በሽታ በቅርብ ያገገሙ በቂ ምግብ የማይመገቡሆስፒታል አይሲዮ ውስጥ ተኝተው የህክምና ክትትል ሲያገኙ የቆዩ ሰዎች ከአንዳንድ ኬሚካል እና መራዥ ንጥረ ነገሮች ጋር ንክኪ የነበራቸው አይነቶችእንደ መንስኤቸው የሳንባ ምች አይነቶች ይለያያሉ

የባክቴሪያ ሳንባ ምች፡ ስትሬፕቶኮከስ

ኒሞንያ(Streptococcus pneumoniae) የሚባለው ባክቴሪያ የሳንባ ምች ቀንደኛ መንስኤ ነው። ነገር ግን የተለያዩ ባክቴሪያዎች የሳንባ ምች ሊፈጥሩ ይችላሉ።

የቫይረስ ሳንባ ምች፡ ይህ የምች አይነት በአርኤስቪ ቫይረስ፣ ኢንፍሉዌንዛ ኤ እና ቢ ምክንያት ሊፈጠር ይቻላል።አስፒሬሽን ኒሞንያ፡ ይህ የምች አይነት ምግብ ወይም ፈሳሽ ወደ ሳንባ ሲገባ የሚፈጠር ነው። ተላላፊ አይደለም።የፈንገስ ሳንባ ምች፡ ይህ የምች አይነት በቮሲዲሎይድስ(Coccidioides) የፈንገስ አይነት ሊፈጠር የሚችል ምች ነው።

የሆስፒታል ሳንባ ምች፡ ሌላ በሽታ በምንታከምበት ወቅት በመተንፈሻ መሳሪያ እገዛ ከሆነ የምንተነፍሰው ሳንባ ምች ሊከሰት ይችላል መንስኤው ምንም ሆነ ምን ምልክቶቹ ግን ተመሳሳይነት አላቸው።

## መከላከያ መንገዶች

የባክቴሪያ ሳንባ ምችን ለመከላከል ሁለት የክትባት አይነቶች አሉ። ፕሬቭናር እና ኒውሞቫክስ። እነዚህ ክትባቶች ከተለያዩ የምች ኢንፌክሽኖች ስለሚከላከሉ ለልጆችም ሆነ ለአዋቂዎች የሚመከሩ ናቸው።

ከክትባቶቹ በተጨማሪ ዶክተሮች የሚከተሉትን መከላከያዎች እንድንከተል ይመክራሉ።

አዘውትሮ እጅን መታጠብ፤ ሲያስነጥሱ ወይም ሲያስሉ አፍን መሸፈን፤አለማጨስ፤የተመጣጠነ ምግብ መብላት፤በሳምንት 5 ግዜ አካል ብቃት እንቅስቃሴ ማድረግ፤ኒሞኒያ ካለባቸው ሰዎች ሳል እና አክታ መራቅ፤

# ሳይነስን ለማከም 5 ቀላል መንገዶች

ሳይነስ፡ - በሰውነታችን ውስጥ ያሉ አየር የሚንሸራሸርባቻን ክፍሎችየሚያጠቃ የህመም ዓይነት ነው፡፡ ህመሙ ሶስት ደረጃዎች ያሉት ሲሆን፣አኪዩት፣ሰብ አኪዩት እና ክሮኒክ ሳይነስ(ሲኖሳይተስ) በመባል ይታወቃሉ፡፡የህመሙ መነሻዎች የቫይረስና ባክቴርያ ኢንፌክሽን ሲሆን፣አልፎ አልፎየሰዎች አፈጣጠር ወይም አናቶሚ ለህመሙ መከሰት ሰበብ ይሆናል፡፡

ከሁሉም በላይ ግን ለበሽታው መከሰት ምክንያት እየሆነ ያለው አለርጂነው፡፡ይህም አለርጂክ ሳይኖሳይተስ በመባል ይታወቃል፡፡ይህንን ህመም ለመከላከል የሚጠቅሙ 5 ቀለላልና ተፈጥሮአዊ መንገዶች የሚከተሉት ናቸው፡-

1. ቀይ ጥሬ ሚጥሚጣ፡-ቃጠሎን መቋቋም እስከቻሉ ድረስሳይኖሳይተስን ለማከም ወደር የማይገኝለት ተፈጥሮአዊ መድሃኒት ነው፡፡አፍንጫን በፍጥነት በማጽዳት ውስጡ ላይ ያለን እብጠት በማጥፋት እፎይታን ይሰጣል፡፡በሚመችት መንገድ አዘጋጅተው መጠቀም ይችላሉ፡፡

2. ዕርድ፡- ዕርድ በውስጡ ከርከሚን የሚባል እብጠትና የመለብለብስሜትን ሚከላከል ንጥረነገር አለው፡፡ይህ ንጥረነገር ሳይኖሳይተስንከመከላከሉም በተጨማሪ የሰውነትን የበሽታ መከላከል አቅም ከፍያደርጋል፡፡500mg የእርድ ዱቄትን በውሀ በማዋሀድ ወይም በእንክብልመልክ በቀን ሁለት ጊዜ መውሰድ ጠቃሚ ነው፡፡

3. ነጭ ሽንኩርት፡-ነጭሽንኩርትን በብዛት መመገብ እጅግ በርካታየጤና ትሩፋቶችን ያስገኛል፡፡በውስጡ አሊሲን የተሰኘ ንጥረነገር የያዘሲሆን፣ይህ ንጥረነገር ቫይረስ ፣ባክቴርያና ፈንገስን የሚከላከል በመሆኑ ለሳይኖሳይተስ ኢንፌክሽን ፍቱን መድሃኒት ነው፡፡በቀን ውስጥ ከሁለትእስከ ሶስት ራስ ፍሬሽ ነጭ ሽንኩርትን በማንኛውም ዓይነት መመገብ ከፍተኛ ውጤት ያስገኛል፡፡

4. ቀረፋ፡-በውስጡ ጎጂ የሆኑ ሳይኖሳይተስን የሚያስከትሉ ባክቴርያዎችን የሚገድል ኬሚካል ስላለው ከግማሽ የሻይ ማንኪያ እስከአንድ የሻይ ማንኪያ ድረስ ከወለላ ማር በመቀላቀል በአንድ ብርጭቆ ለብ ያለ ውሀ መጠጣት ፍቱን መድሃኒት ነው፡፡

5. ዝንጅብል፡- ዝንጅብል በውስጡ ፀረ-የአፍንጫ ፈሳሽ እና ፀረ-መለብለብና እብጠት ኬሚካሎችን በውስጡ ስለያዘ እንዲሁም የሰውነትን የበሽታ መከላከል አቅም ስለሚጨምር ሳይኖሳይተስን ለመከላከልይረዳል፡፡ የዝንጅብል ሻይን ከሎሚ ጭማቂ ጋር ቀላቅሎ መጠቀምለሳይኖሳይተስ ፍቱን መድሃኒት ነው፡፡

ምንጭ፡- `STICETHIOPIA` and `ናቹራል ኪዩርስ ኤንድ ናቹራል ሬሜዲስ ዶት ኮም



# የማሳጅ ጠቀሜታ

የሰውነት ንክኪ ከምንም በላይ ሀይል እንዳለው የሕክምና ባለሙያዎች በተለያየ ጊዜ የሚናገሩት ነው፡፡ ገና ሕፃን ሆነን እናታችን ስትደባብሰን የሚሰማን የደስታ ስሜት የንክኪ ኃይል መገለጫ ነው፡፡ ካደግንም በኋላ መደባበስን እንናፍቃለን፡፡ ሰውነት ዘና እንዲልና ጡንቻዎች እንዲፍታቱ ሰውነትን መታሸት ወይም ማሳጅ ፍቱን ህክምና ነው፡፡ሰውነትን መታሸት በጥንት ጊዜ እንደህክምና ዘዴ ይቆጠር ነበር፡፡ ጡንቻ ሲሸማቀቅ፣የደም ዝውውር ሲዛባና ህመም ሲሰማ ሰውነትን መታሸት የተለመደ ነበር፡፡ሰውነትን መታሸት እንደየሰው ፍላጎት ይለያያል፡፡ለምሳሌ እግርን፣ጀርባን፣ደረትን ብቻ መታሸት የሚፈልግ ሰው አለ፡፡ የሚከተሉትን የተወሰኑ የማሳጅ አይነቶች ናቸው፡፡

## የሆድ ማሳጅ

ይህ በሆድ አካባቢ ያለን ህመም ለማስታገስ ይረዳል፡፡ ይህ የውስጣዊ ሰውነት ማሳጅ በመባል ይታወቃል፡፡ ሲጀምሩት አድካሚና የሚያም ቢሆንም ለሆድ በሽታ ፍቱን መድሀኒት ነው፡፡ በሽታ ለመከላከልም ጥሩ ነው፡፡

## የአንገት ማሳጅ

በአንገት አካባቢ ያሉ ጡንቻዎች እንዲፍታቱ ያደርጋል፡፡ለአንገት ህመምና ስትራፖ ወደር ያልተገኘለት ዘዴ ነው፡፡

## ለጭንቀት የሚረዳ ማሳጅ

ጭንቀት፣ውጥረትንና ሌሎች ተመሳሳይ ችግሮችን ለመቅረፍ የሚደረግ ማሳጅ ነው፡፡

## የጡንቻ ማሳጅ

ስፖርተኞች ጉዳት ሲደርስባቸውና ሰዎች ከኮማ ሲነቁ የሚደረግላቸው የማሳጅ አይነት ነው፡፡

## የእግርና የእጅ ማሳጅ

ይህ ሰውነት በጣም እንዲዝናና የሚደረግ ከመሆኑም በላይ ራስን በራስ ማሸት መቻሉ ተመራጭ ያደርገዋል፡፡በእግርና በእጅ ላይ የሚከሰት ህመምን ወይም ስትራፖን ለማስወገድ ፍቱን ነው፡፡

## የአከርካሪ አጥንት ማሳጅ

ይህ አከርካሪ አጥንት ቀጥ እንዲል ያደርጋል፡፡በተለይ ከትከሻቸው ጎበጥ ላሉ ሰዎች ቀና እንዲሉ በማድረግ ቁመት ይጨምርላቸዋል፡፡ከሌሎቹ ይልቅም ህመም ያለው ይሄው የማሳጅ አይነት ነው፡፡

ሰውነትን ለማዝናናት የሚደረግ ማሳጅ

ይህ በጣም በብዙ ሰዎች ዘንድ የተለመደና በጣም አስደሳቹ ዘዴ ነው፡፡ህመም ሳይሆን ለመዝናናት ስለሆነ በጣም አስደሳች ነው፡፡

## የመገጣጠሚያ ማሳጅ

የአጥንቶች መገጣጠሚያዎች በአግባቡ እንዲሰሩ ይረዳል፡፡መገጣጠሚያዎች ዘና እንዲሉ ያደርጋል፡፡በጣም የሚያዝናና ና አስደሳችም ነው፡፡

## ማሳጅ ስናደርግ ልናደርጋቸው የሚገቡ ነገሮች

1. ማሳጅ ጡንቻን ከማፍታታት በተጨማሪ ጭንቀትን ለማስወገድ ይረዳል፡፡ስለዚህ ራስን ዘና ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ለዚህም በምን ታሸበት ጊዜ በደንብ መተንፈስ ይገባል፡፡ራሳችንን ወይም ሀሳባችንን ጥለን መታሸው ጠንጴዛ ላይ መተኛት፡፡የሚያስጨንቀንን ነገር ወደጎን በመተው ራስን ለማዝናናት መሞከር፡፡

2.በምንታሸበት ጊዜም ማውራት ባይከለከልም ባናወራ ይመረጣል፡፡ምክንያቱም ሀሳብን ለመሰብሰብ ያዳግታልና፡፡ሀሳባችንን ካልሰበሰብን ደግሞ ጡንቻዎቻችን አይፍታቱም፡፡

3.ሰውነታችንን የሚያሸው ባለሙያ ካለተመቸን ወይም የማንፈልገው ቦታ ከነካን በግልፅ መናገር ያስፈልጋል፡፡ አእምሮንና ሰውነትን የምናዝናናበት እንጂ የምንጨነቅበትና የምንሰጋበት አይደለምና፡፡

4.አይንን መጨፈን፣በንክኪ በሚሰማን የስሜት አይኖች ብቻ መመልከት፡፡ሰውነት በሚታሸበት ጊዜ አይንን መጨፈን አንድ ሰው በአእምሮው የሚያወጣውና የሚያወርደው ነገር ያበቃና ሰውነቱ የሚሰማውን ደስታ ማሰላሰል ይጀምራል፡፡

5.ለሰውነት መታሻችን መምረጥ፡፡ ሽታ ያላቸው ቅባቶች የማይስማሙ ከሆነ አስቀድሞ መናገር፡፡በምትኩም የሚስማ ሙንን መጠቀም፡፡

## ከማሳጅ በኋላ ልናደርጋቸው የሚገቡ ነገሮች

1. ብዙ ውሀ መጠጣት፡፡ይህም ሰውነት በሚታሸበት ጊዜ የማያስወጣቸውን የተበረዙ ነገሮች ለማስወጣት ይረዳል፡፡ እንዲሁም ሰውነትን ለማቀዝቀዝ ፍቱን ነው፡፡

2.ሰውነታችንን ከታሸን በኋላ ለ20 ደቂቃ ማሳረፍ፡፡ለምሳሌ አጭር ዎክ ማድረግ፣ሊያም እረፍት ማድረግ፡፡ ይህም የተፍታታው ሰውነታችን እንዲረጋጋ ያድርገዋል፡፡

3.ከታሸን በኋላ ሉብ ባለ ውሀ ገላን መታጠብ እንድንታደስ ያደርገናል፡፡

4.ከተቻለ ሰውነትን ከታሹ በኋላ በእግር መጓዝ፡፡ይህም ዘና ያለው ሰውነትን እንድንላመድ ያደርገናል፡፡

## kiss stories

ቤተሰቦቻችን ባህልና ወግ አጥባቂ የሚባሉ አይነት ናቸው፡፡ታዲያ እኛ ቤት ቴሌቪዥን የሚከፈተው ለዜና ብቻ ነው፡፡ ዘፈን ከመጣ እንኳን ቶሎ እንዲዘጋ ይደረጋል፡፡ ፊልም ማየትማ በጣም ያስቆጣል፡፡ ከዚህ ካለፈም ሊያስገርፍ ይቻላል፡፡ እድሜያችን ከፍ ካለ በኋላ ግን ወላጆቻችን ቤት በማይኖሩበትና ርቀው መሄዳቸውን ስናውቅ ፊልም እያየን እያለ ወንድሜ መምጣቱን ስናውቅ ቲቪውን ሳናጠፋ መኝታ ቤት ገባን፡፡ ወንድሜ ከአሁን አሁን ጠራኝ እያልኩ ተሳቅቄ አጮልቄ እያየሁ ነው፡፡ ወንድሜ ሶፋው ላይ ተደላድሎ ተቀምጦ ፊልሙን ማየት ጀመረ፡፡ ፊልሙን የከፈተው ማን ነው ሳይለን ቀረ፡፡

እንደውም ከንፈሯ ተለቅ ያለ አፍሪካዊት ሴት ከነጭ ጋር ስትሳሳም ያየውን በማድነቅ «እንደዚህ በነፃነት ገመጣት» እያለ ማየቱን ቀጠለ፡፡ ከዛን ቀን በኋላ ከንፈሮ ወፍራም ሴት ካየሁ አባቴን አስታውሳለሁ፡፡ አንድ ቀን ከየት መጣች ሳልል አንዲት ሞንዳላ የቤት ሰራተኛ ከትምህርት ቤት ስመለስ ቤት ውስጥ አገኘኋት፤ ልጅቱ ገጠሬ ነገር ነች፤ ግን ታዛዥና ተግባቢ ናት፤

ታዲያ አንድ ቀን ከትምህርት ቤት እንደመጣሁ በጣም እንደሞቀኝና ገላዬን መታጠብ እንደምፈልግ ነገርኳት፤ ከዚያ ውሃ እንድታሞቅልኝና ሲፈላ እንድትጠራን ነግሬያት ወደ ሳሎን ገብቼ ፊልም ማየት ጀመርኩ፡፡ በዕለቱ ቤት ውስጥ ማንም ስላልነበረ የፍቅር ፊልም ነበር የከፈትኩት፡፡ ፊልሙን እያየሁ ሳለ በሩን ቀስ ብላ ከፍታ ‹ውሃው ሞቋል› አለችኝ፤ እሺ ብዬ ፊልሜን ማየት ስቀጥል ሰራተኛዋ ቆማ ፊልሙን ማየት ጀመረች፡፡ የፊልሙ ተዋንያን መሳሳም ሲጀምሩ ‹እንዴ!› ብላ በሩን ከፍታ ወጣች፤ ፊልም እንዳለቀ ወደ መታጠቢያ ስገባ እየሳቀች ነበር፡፡

ምነው ስላት ‹ደግሞ ሰዎቹ ምንድነው የሚያደርጉት › አለችኝ፡፡ አሁን መግቢያ ቀዳዳ አገኘሁ ብዬ ነይ ላሳይሽ ስለት እሺ ብላ መጣች፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜ የሞንዳላ ሴት ወፈራም ከንፈር የሳምኩት በዚህ አጋጣሚ ነበር፡፡ ሄኖክ አበበ (ከአዲስ አበባ)



# አራቱ የወላጅነት ፈተናዎች

ወላጆች እንደልጆቻቸው ጸባይ በተለያዩ መንገዶች ይፈተናሉ:: ዕድለኛ የሆኑትና በራሳቸው አስተሳሰብ ልጆቻቸውን ለመምራት በቁርጠኝነት የሚተጉት ወላጆች ድካማቸው የተሻለ ይሆናል:: በርግጥ እያንዳንዱን ወላጅ ብትጠይቁት በልጅ አስተዳደግ የተለያዩ ፈተናዎች እንደሚገጥሙት ይነግራችኋል:: ከጾታ ልዩነት ጀምሮ፣ የጤና ኹኔታ፣ ተፈጥሯዊ ጸባይ፣ ማኅበራዊ ትስስርና የተለያዩ ምክንያቶች አንዱ ልጅ ከሌላው ልጅ የበለጠ አስቸጋሪ እንዲኾን ሊያደርጉት ይችላሉ::

ለመኾኑ ልጅ ወልደው ለማሳደግ ዝግጁ የኾኑ ወላጆች በዋነኝነት ትኩረት ሊያደርጉባቸው የሚገቡት ጉዳዮች ምን ምን ይኾኑ?

## 1. ጤና

የጤና ጉዳይ ከጨቅላነት ዕድሜ ጀምሮ በተለያዩ የዕድሜ እርከኖች የሚገጥም ሊሆን ይችላል:: ስለዚህ ወላጆች በየትኛውም አጋጣሚ ለሚፈጠሩ የልጆቻቸው የጤና እክሎች ዝግጁ ሊሆኑ ይገባል:: ህፃናት የሚመገቧት እያንዳንዷ ምግብ ሳትቀር ለጤናቸው ተስማሚ መሆኗን ማረጋገጥ፣ የንፅህናቸው ሁኔታ፣ የሚጫወቱበት አካባቢና ሌሎችም ነገሮች ለጤናቸው መታወክ የራሳቸው አስተዋፅኦ ስለሚኖራቸው ወላጆች በንቃት የልጆቻቸውን ሁኔታ መከታተል የውዴታ ግዴታቸው ሊሆን ይገባል:: የራስዎን ጤንነት በሚጠብቁት ልክ ለልጆችዎም ጎጂውን ከጠቃሚው በመለየት በደስተኝነትና በጤናማነት ያድጉ ዘንድ መሠረታዊውን የጤና ክትትልና እንክብካቤ ሳይሰለቹ ያድርሷቸው::

## 2. ትምህርት

የትምህርት ጉዳይም ወላጆች ለልጆቻቸው ማሟላት ከሚገባቸው መሠረታዊ ግዴታዎች መካከል አንዱ ነው:: ትምህርት ቤቶች የቀለም ዕውቀትና ማኅበራዊ ክህሎቶች ለማስጨበጥ የሚረዱ የልጆች ሁለተኛ ቤቶች ናቸው:: ግንኙነታቸውን ለማጎልበትና ጥሩ ፀባይ ለመቅሰምም ይጠቅሟቸዋል:: ስለዚህ ጥራቱን የጠበቀ ትምህርት የሚያገኙባቸውን ዕድሎች በማመቻቸት ለነገው የልጆችዎ ሕይወት ዛሬን በትጋት ኃላፊነትዎን ይወጡ::

## 3. ፀባይ

እንደወላጅ ሁላችንም ልጆቻችን ‹ትናንሽ መላእክት› ቢሆኑልን እንመኛለን:: ነገር ግን በእኛም ይሁን በአካባቢያችን ተፅዕኖ ምክንያት ፀባያቸው አስቸጋሪና ከቁጥጥር ውጪ ሆኖ ፈተናችንን የሚያከብድባቸው አጋጣሚዎች ይፈጠራሉ:: በዚህ ወቅት ራስን መለስ ብሎ መጠየቅ ተገቢ ይሆናል:: ‹ለመሆኑ ልጄ ከኔ ፀባይ ምን ይማራል?፤ አካባቢዬስ ልጄ መልካም ፀባይ ኖሮት እንዲያድግ የሚኖረው አስተዋፅኦ ምን ያህል ነው?› የሚሉትን ጥያቄዎች በማንሳት የችግሩን ምንጭ ይገንዘቡ:: ከጓደኞቻቸው ማንነት ጀምሮ፣ የሚመርጧቸው የጨዋታ ዓይነቶችና ከቴክኖሎጂ ጋር ያላቸው ቅርርብ በበጎም ሆነ በመጥፎ እንዲቀረፁ ያደርጋሉና በልዩ ትኩረት መከታተል አስፈላጊ ነው::

## 4.የቁጥር ጉዳይ

የአንድ ልጅ እናት ወይም አባት መሆን አንድ ጊዜ በሙሉ ልብ ተቀብለው በደስታና ኃላፊነትን በመወጣት በንቁ ስሜት የሚፈፅሙት የወላጅነት ተግባር ነው:: ልጆችዎ በተቀራራቢ ዕድሜ የሚገኙና ቁጥራቸው ከአንድ በላይ ሲሆን ግን ፈተናዎም መጠኑ ይጨምራል:: ለአንዱ የገዙትን ነገር ለሌላዋ አለመግዛት በልጅ ዘንድ አድሏዊ ሆነው እንዲታዩ ስለሚያደርግ ምንም ዓይነት ማበላለጥ ውስጥ እንዳይገቡ ይጠንቀቁ:: ልጆችዎ ከእርስዎ በሚያገኙት ፍቅር፣ በየዕለቱ በሚደረግላቸው እንክብካቤና በተለያዩ መንገዶች አንዳቸው ሌላቸውን በልጠው ለመገኘት ስለሚጥሩ እርስዎ ከማገዝና መንገድ ከመምራት ባለፈ በፉክክራቸው መሐል ባይገቡ ይመረጣል::

በአጠቃላይ ጥሩ ወላጅ መሆን ፈተናው እጅግ ከባድ ነው:: ለሚኖርባት ዓለም ብሎም ለተወለደበት ማኅበረሰብ አንዳች ቁም ነገር ማበርከት የሚችል ልጅ እንዲኖርዎ ጥሩ ወላጅ ለመሆን ራስዎን ያለማምዱ:: ጥሩ ወላጅ የልጆቹን ቁሳዊና መንፈሳዊ ፍላጎቶች አሟልቶ በዕለት ተዕለት ሩጫቸው በጎውን መንገድ እያሳየ ወደ አሸናፊነት ሰገነት የሚያወጣ ነው:: የእነኚህ ሁሉ ፈተናዎች ድል የሚሆነውም እርሱ ነውና ለፈተናዎቹ አሁኑኑ ታጥቀው ይነሱ::

ምንጭ:- Marriage.com

ከሰሞኑ

አርሂቡ

# ኬር አውድ የባህል ምግብ አዳራሽና ምሽት ቤት ተመርቆ ስራ ጀመረ

በውቢቷ ሀዋሳ ከተማ የኬር አውድ ኢንተርናሽናል ሆቴል እህት ድርጅት የሆነው ኬር አውድ የባህል ምግብ አዳራሽና የምሽት ቤት ተመርቆ ስራ መጀመሩ ተሰማ፤

የኬር አውድ ኢንተርናሽናል ሆቴልና የባህል ምግብ አዳራሽ ባለቤት አቶ ሙራድ አሂ እንደገለፁት የባህል ምግብ አዳራሹ እስከ 15 ሚኒሊየን ብር ወጪ የተደረገበትና የሁሉንም የሀገራችን ብሔር ብሔረሰቦች ባህልና ትውፊት ሊያሳይ በሚችል መልኩ የተገነባ እንደሆነ ተናግረዋል፡፡የባህል ምሽት ቤቱ መከፈት ለሀዋሳና አካባቢዋ ነዋሪዎች እንዲሁም ሀዋሳን ሊጎበኙ ለሚመጡ የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር ቱሪስቶች አይነተኛ መዝናኛ ስፍራ እንደሆነ ተመልክቷል፡፡ኬር አውድ የባህል ምግብ አዳራሽና ምግብ ቤት ከ90 በላይ ለሚሆኑ ሰራተኞች የስራ ዕድል የፈጠረ ሲሆን ከፍተኛ የመንግስት ለስልጣናት፤ ታዋቂ ሰዎችማ ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች በተገኙባት ተመርቋል፡፡

በባህል ምሽት ቤቱ በየዕለቱ ከሰኞ እስከ ሰኞ የተለያዩ ታዋቂ አርተስቶችን ያሳተፈ የሙዚቃ ትርኢት እንደሚቀርብ የዝግጅቱ አስተባባሪ አርቲስት ታምሩ ብርሃኑ ለዝግጅት ክፍላችን አስታውቋል፡፡



# ከፌስ ቡክ ማሕደር



የሱሪ

ሌላኛው

ገልግሎት?



## የኪነ ጥበብ ባለሙያው ጌታቸው ደባልቄ ተሸኙ

አንጋፋው የኪነ ጥበብ ባለሙያ ጌታቸው ደባልቄ የቀብር ስነ ሥርዓት የካቲት 24 ቀን 2011 በቅድስት ስላሴ ካቴድራል ተፈፅመ፡፡ ‹ተንቀሳቃሽ ቤተ መፅሐፍት› በሚል ቅፅል ስም ይታወቁ የነበሩት አንጋፋው አርቲስት ጌታቸው ደባልቄ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቴአትር ሲከፈት ከ1948 ዓ.ም ጀምሮ በቴአትር ቤቱ ይቀርቡ በነበሩ ቴአትሮችና የሙዚቃ ትርኢቶች ላይ ሲሳተፉ ነበር፡፡ በተለይም ቴአትር ቤቱ ሲመረቅ ‹ዳዊትና ኦሪዮን› በተሰኘው ቴአትር ላይ በዋና ተዋናይነት መሳተፋቸው ተገልጧል፡፡

አርቲስት ጌታቸው ደባልቄ የረዥም ዘመን አገልግሎታቸውን መነሻ በማድረግ በ1994 ዓ.ም በቴአትር ሙያ ላበረከቱት አስተዋፅኦ የስነ ጥበባትና መገናኛ ብዙሃን የሽልማት ድርጅት የረዥም ዘመን ተሸላሚ አድርጎ የክብር ዲፕሎማና የ20 ሺ ብር ሽልማት እንዳበረከተላቸው ይታወሳል፡፡

የኪነ ጥበብ ባለሙያው ጌታቸው ደባልቄ የካቲት 22፣ 2011 ምሽት ነው በ83 ዓመታቸው ያረፉት። ጌታቸው ደባልቄ ለረጅም ዓመታት በትያትር ሙያ ላይ ያሳለፉ ሲሆን፥ በጸሐፊ ተውኔት በአዘጋጅነት ሰርተዋል። ለታዋቂ ድምጻውያንም የግጥምና የዜናማ ድርሰት ሰርተዋል፡፡

## በትግርኛ ዘፈኖቹ የሚታወቀው አርቲስት አሚር ዳውድ የቀብር ስነ ስርዓት ተፈፀመ

በትግርኛ ዘፈኖቹ የሚታወቀው አርቲስት አሚር ዳውድ የቀብር ስነ ስርዓት ተፈፀመ፡፡አዲስ አበባ የካቲት 22፣ 2011 ምሽት በመቐለ አይደር ሆስፒታል ህይወቱ ያለፈው በትግርኛ ዘፈኖቹ የሚታወቀው አርቲስት አሚር ዳውድ የቀብር ስነ ስርዓቱ ተፈጽሟል፡፡

አርቲስት አሚር በቅርቡ ከ400 መቶ ሺህ ብር በላይ ያወጣበትን ሲዲ በትግራይ ክልል ለሚገኙና ከተለያዩ ክልሎች ለተፈናቀሉ የክልል ተወላጆች እንዲውል አበርክቷል።በተለይም አይሞቱም ጀጋኑና በሚለው ስራው የሚታወቀው አርቲስቱ የግጥምና የዜማ ደራሲ ሲሆን፥ ባለትዳርና የሁለት ሴት ልጆች አባት ነበር፡፡

ከሰሞኑ

አርሂቡ

# መገበያያ ገንዘቦች ስያሜዎቻቸው

የመገበያያ ገንዘቦች እንደ የሃገራቱ ነባራዊ ሁኔታ የተለያየ ስያሜና መጠሪያ ይሰጣቸዋል።የገንዘቡ የስያሜ ምንነት እና ትርጉምም ከሃገራቱ ነባራዊ ሁኔታ ጋር የተያያዘ ስለሆኑ የኦክስፎርድን መዝገበ ቃላት ምንጭ ያደረገው የዊ ፎረም ድረ ገጽ መረጃ ያሳያል።ድረ ገጹ መጽሃፉን ጠቅሶ ባወጣው መረጃ እያንዳንዱ የመገበያያ ገንዘብ መጠሪያ ስያሜውን እንዴት እንዳገኘ ያትታትል፤ ዝርዝሩን ከዚህ በታች ይመልከቱት።

ዶላር፡- በአሜሪካ፣ አውስትራሊያ፣ ካናዳ፣ የፊጂ ደሴቶች፣ ኒውዝላንድ እና ሲንጋፖርን ጨምሮ በተለያዩ ሃገራት ለመገበያያነት የሚውል ገንዘብ ነው።

የማዕድን መገኛ ስፍራ የሆነውን ጆዓኪምስታል ወይም የጆዓኪምን ሸለቆ የሚለውን ጀርመንኛ ቃል መነሻ ያደረገ መሆኑን ይጠቅሳል። ለዚህ ደግሞ በስፍራው የተገኙ ሳንቲሞች የጆዓኪምስታል የሚል ስያሜን ይይዛሉ፤ ይህን እጥር ባለ ቃል ሲገልጹት ደግሞ ታለር ይሉታል።

የረጅሙ ጀርመንኛ ቃል መጨረሻ ደግሞ ዶላር ሆነ ይላል የገጹ ማጠቃለያ።

የስፔን መገበያያ ገንዘብ ፔሶ፡- ይህ ቃል በሃገሬው ክብደት ወይም መለኪያ የሚል ስያሜን ይዟል።

ሊሬ፡- የጣሊያንና የቱርክ መገበያያ ገንዘብ የሆነው ሊሬ ደግሞ ሊብራ ከሚለው የላቲን ቃል የመጣ ሲሆን፥ ፓውንድ የሚል ትርጓሜን ይይዛል።

ማርክ፡- ከዩሮ በፊት የነበረው የሆላንድ እና ፊንላንድ መገበያያ ገንዘብ ማርክ ከክብደት መለኪያዎች ስያሜዎቻቸውን እንዳገኙ ይነገራል።

ሪያል፡- በአብዛኛው የዓረብ ሃገራት በተለይም ኳታር፣ ሳዑዲ፣ የመን፣ አማን እና ኢራን የሚጠቀሙት ሪያል ስርዎ መሰረቱ የላቲን ቃል ነው።

ሬጋሊስ የሚለው የደቡብ አሜሪካ ቃል ንጉሳዊ የሚል ትርጓሜን ይይዛል።

ራንድ፡- የደቡብ አፍሪካው መገበያያ ገንዘብ ራንድም እንደ ዶላር ሁሉ የማዕድን ስፍራን መነሻው ያደረገ ነው።

ዊት ዋተር ስራንድ በመባል የሚታወቀውና በወርቅ ማዕድን የበለጸገው ስፍራ በሆላንዶች የራንድን ስያሜ አግኝቷል።

የቻይና ዩዓን፣ የጃፓን የን እና የኮሪያዎች ዎን፡-

የቻይናዋ ￿ ምስል ክብ የሚለውን ትርጉም ይሰጣል፤ ይህም ለአራቱ ሃገራት የመገበያያ ገንዘብ ስያሜ መነሻ መሆኑ ይነገራል።

ክራውን፡- የስካንዲኒቪያን ሃገራት ከላቲኑ ቾሮና ቃል የመነጨውን እና ዘውድ የሚል ስያሜ ያለውን መገበያያ ገንዘብ ይጠቀማሉ።

ስዊድን እና አይስላንድ - ክሮና፣ ኖርዌይ እና ዴንማርክ - ክሮን፣ ስቶኒያ - ክሩን ( አሁን የዩሮ ተጠቃሚ ናት) እና ቼክ ሪፐብሊክ ኮሩና የዚህ ተጠቃሚ ናቸው።

ዲናር፡- ጆርዳን፣ አልጀሪያ፣ ሰርቢያ እና ኩዌት ዲናርን በመገበያያነት የሚጠቀሙ ሃገራት ናቸው።

ዲናር ዲናሪየስ ከሚለው የላቲን ቃል የመጣ ሲሆን፥ ዲናሪየስ በጥንታዊት ሮም ጥቅም ላይ ይውል የነበረ የብር መገበያያ ገንዘብ ነው።

ሩፒ፡- በባለሙያ ተቀጥቅጦ ወይም ተጠፍጥፎ የተሰራ የብር መገበያያ ገንዘብን ለመግለጽ የሚውለው ሩፒ የህንድ እና ጎረቤቶቿ መገበያያ ገንዘብ ነው።

ፓውንድ፡- የብሪታንያ መገበያያ ፓውንድ ከላቲኑ ቃል ፓውንደስ ስያሜውን ወርሷል።

መለኪያ ወይም ክብደት የሚለውን ስያሜም ይይዛል፤ ግብጽ፣ ሊባኖስ፣ ደቡብ ሱዳን እና ሶሪያም የመገበያያቸው ስያሜ ፓውንድ ነው።

ሩብል፡- የሩሲያ እና ቤላሩሱ መገበያያ ገንዘብ ለብር ክብደት መለኪያነት ከዋለ በኋላ ስያሜውን አግኝቷል።

ዝሎቲ፡- የፖላንዱ ዝሎቲ ቃል መነሻ ደግሞ በሃገሬው ቋንቋ ለወርቅ የተሰጠው ትርጓሜ ነው።

ፎሪንት፡- የሃንጋሪው መገበያያ ገንዘብ ፊዮሪኖ ከሚለው የጣሊያኗ ፍሎረንስ የወርቅ መገበያያ ገንዘብ ስያሜውን ወስዷል።

ሪንግ ኢት፡- የማሌዥያ መገበያያ ገንዘብ ሲሆን፥ ስያሜው ሃገራት ወንበዴዎች ተመሳሳይ ገንዘብ ሰርተው እንዳይጠቀሙበት የሚከተሉት መከላከያ ዘዴ መጠሪያ ነው። ይህም በሃገሬው ቋንቋ ሪንግ ኢት የሚል ቃልን ይይዛል።

## ስኮላርሺፕ ለተማሪዎች

በዚህ ዓምድ ላይ የሚወጡ የነፃ የትምህርት ዕድሎችን የምትከታተሉ አንባቢያን እንዴት ፎርሙን መሙላት እንደለባችሁ በተደጋጋሚ ጠይቃችሁናል፡፡ በመሆኑም ማንኛውም ሰው በዚህ ገጽ ላይ ያለውን የመረጠውን ዩኒቨርሲቲ ስም በጎግል ላይ በመፃፍ ሰርች ቢያደርግ የምዝገባ ፎርሙና ሙሉ መረጃ የሚያገኝ እንደሆነ እንገልፃለን፡፡

Apply Now with GermanyScholarships.com – Free Application Help

Adelaide Scholarships International (ASI) Scholarships in Australia, 2019-2020

University of Adelaide, Australia

Application Deadline: February 15, 2019 and April 30, 2019

Apply Now

Saltire International Scholarships at Scottish Higher Education Institutions in UK, 2019

Scottish Government and Scottish Higher Education Institutions, UK

Scholarships are available to citizens of the following countries: Canada, China (including Hong Kong), India, Japan, Pakistan, and the USA

Application Deadline: May 26, 2019

Apply Now

Freeform Media Relations/PR Internship (DATG) CA-Summer 2019

Disney, Inc.Application Deadline: Ongoing

Apply Now

PhD Scholarships in Computer Science and Informatics at Cardiff University in UK, 2019

Cardiff University, UK

Application Deadline: April 23, 2019

Apply Now

Sister Cities International Student's Scholarship at East Tennessee State University in USA

East Tennessee State University, USA

Application Deadline: March 1, 2019

Apply Now

## ብሔራዊ እርቅ.....

ከገጽ 6 የዞረ

ክፍሎች ግብአትን ያካተተ፤ ግልጽና የህዝብ እምነትን የሚያዳብር ሆኖ መገኘት ይኖርበታል።

የእርቅና ሰላም ኮሚሽን አባላት ምርጫ ነጻ መሆንን ፣ ብቃትና ታአማኒነታቸውንም ለማረጋገጥ የኮሚሽኑን አባላት ምርጫ በመንግስት መሪ በብቸኝነት ወይም በግብታዊነት በሚሰጥ ሀላፊነት በተወሰኑ ምርጥ ግለሰቦች አማካሪነት የሚካሄድ ሳይሆን የሀገሪቱን ታሪካዊና ተጨባጭ የሰብአዊ መብት ጥሰቶችና የተወሳሰቡ ችግሮች (ቅራኔዎች) በጥንቃቄ ባገናዘበ ሁኔታ የተለያዩ ባለድርሻዎችን ያሳተፈ አስመራጭ ኮሚቴ በኮሚሽን አባላቱ ምርጫ ላይ ሀላፊነት ወስዶ በቀጥታ ሊመራው እንደሚገባ የተለያዩ ሀገሮች ልምድ አሳይቷል።

የዚህ አይነት መሰረት ሳይመቻች ከፍ ያለ ታማኒነትን ማግኘት፣ ሰላባ የሆኑ ሁሉ ሂደቱንና ተቋሙን "ለእኔም ፍትህን ያሰገኛል" ብለው ኮሚሽኑን እንዲተባበሩ ማድረግ እጅግ አስቸጋሪ ይሆናል፡፡ ይህ ካልሆነ ደግሞ የእርቀሳላሙ ሂደት ገና ከመጀመሩ ይከሽፋል፣ የግጭትና የጦርነት አዙሪትም ይቀጥላል።

## የተለያዩ ሀገሮች ልምድ እንደ ማሳያ

ብሄራዊ እርቅን በተሳካ ሁኔታ በመተግበር ከሚታወቁት ሂደቶች ውስጥ የደቡብ አፍሪካው የእውነትና የእርቅ ኮሚሽን (Truth and Reconciliation Commission TRC) አንዱና አንጋፋውም ነው። ይህን ተግባር በሀላፊነት ለውጤት ያደረሰው ኮሚሽን ምስረት የተካሄደው የተለያዩ ፖለቲካ ድርጅቶችና ሲቪክ ማህበረሰብ ወኪሎች እንዲሁም የገዥው ያአፍሪካ ብሄራዊ ኮንግረስ ( ኤ ኤን ሲ ANC) አባላትን አካትቶ በተዋቀረ ኮሚቴ በጋራ ባካሄዱት የእጩዎች ምርጫ አማካኝነት ነበር። ደቡብ አፍሪካውያን የኮሚሽን አባላትን በመጠቆም ሳይቀር ቀጥተኛ ተሳታፊ ሆነው ነበር። https://www.britannica.com/topic/Truth-and-ReconciliationCommission-South-Africa

እጅግ አሳዛኝና ዘግናኝ በሆነ የዜጎች ሰቆቃና የሰብአዊ መብት ረገጣ ውስጥ ያለፈችው ላይቤሪያም ብትሆን በህዝቧ ውስጥ የደረሰውን ስብራት ለመጠገን የተጓዘችበት የብሄራዊ እርቅና እውነት ጎዳና ሲሆን ይህን ሀላፊነት እንዲመሩ የተመረጡ የኮሚሽን አባላትም የተመረጡት ሶስት ከሲቪክ ማህበረሰቡ የፖለቲካ ድረጅቶች ሁለት ወኪሎች አንድ ከተባበሩት መንግስታት ወኪል እና አንድ ወኪል ደግሞ ከምእራብ አፍሪካ የኢኮኖሚ ማብህበረሰብ (ECOWAS) ተብሎ ከሚታወቀው የምእራብ አፍሪካ ሀገሮች ድርጅት ወኪል የተውጣጣ ሰባት አባላትን ባካተተው ኮሚቴ ነበር https://www.refworld.org/pdfid/473c6b3d2.pdf

የረዥም አመታት የ እርስ በርስ ጦርነትና የብሄር ክፍፍል ስትተራመስ የኖረችው የምእራብ አፍሪካዋ ሴራሊዮን የብሄራዊ እርቅ ኮሚቴ አባላትን ምርጫ ያካሄደው ስድስት ሰዎችን ያካተተ የአስመራጭ ኮሚቴ ሲሆን ይህ አስመራጭ ኮሚቴ የተውጣጣውም ከሚከተሉት ክፍሎች አንድ አንድ ወኪሎችን በማካተት ነበር ፡፡

ከ Revolutionary United Front of Sierra Leone ከተሰኘው የፖለቲካ ስብስብ፤ ከጦር ሀይሎች፣ ከሰብአዊ መብት ድርጅቶች ፎረም፣ የሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ድርጅት ወኪል እንዲሁም የተባበሩት መንግስታት ዋና ጸሀፊ ልዩ መልእክተኛ በኮሚቴው አስተባባሪነት ። በሴራሊዮን ሁኔታ የኮሚሽኑ አባላት ገሚሱ ከሀገር ውስጥ ሎሎች ደግሞ በውጭው ሀገር ከሚገኙ ሴራሊዮናውያን የተዋቀረ ሲሆን በውጭው የነበረውን የኮሚሽን አባላት ምርጫ ያቀነባበረው ደግሞ በጀኔቭ የሚገኘው የተባበሩት መንግስታት የሰብአዊ መብት ከፍተኛ ኮሚሽነር (The Office of High Commissioner for Human Rights (OHCHR ) ጽህፈት ቤት ነበር http://www.sierraleonetrc.org/index.php/national-vision-for-sl

ለማጠቃለል ሁሉም የእኔ ብሎ የሚቀበለው ውጤትን ለማግኘት፣ ተጎጂዎች ያለምንም ፍራቻና ቸልተኖነት በግልጽ የደረሰባቸውን በደል ለማካፈል እንዲችሉ ለማበረታታት ሁሉም ባለድርሻ የተሳተፈበትና አመኔታን የሰጠው ሂደት ተግባራዊ መሆኑ መሰረታዊ ጉዳይ ነው።

## በእኛ ሀገርስ?

በሀገራችን ውስጥ በጠቅላይ ሚኒስቴር አብይ አማካኝነት የእርቀ ሰላም ኮሚሽኑን ለማቋቋም የቀረበው ረቂው አዋጅ በፓርላማው ቀርቦ የፀቀደቀው በታህሳስ 16፣ 2011 (ዲሰምበር 25፣ 2018) ነበር። የኮሚሽኑ አባላት ስም ዝርዝር ለፓርላማው ቀርቦ የጸደቀው ደግሞ በጥር 28፣ 2011 ( በ ፊበርዋሪ 5፣ 2019 )፣ማለትም ባንድ ወር ከሁለት ሳምንት ውስጥ ነበር ማለት ነው።

ከአዋጁ የሚመነጭ ድክመት፡-

የእርቀሰላም ኮሚሽኑን አመራረጥ በተመለከተ በአዋጁ ውስጥ የሚከተለው ሰፍሮ ይገኛል፡፡

## የኮሚሽኑ አባላትና አሰያየም

1/ የኮሚሽኑ አባላት ቁጥር በመንግስት የሚወሰን ይሆናል፡፡

2/ የኮሚሽኑ ሰብሳቢ ፣ምክትል ሰብሳቢ እና ሌሎች አባላት በጠቅላይ ሚኒስቴሩ አቅራቢነት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤቱ ይሰየማሉ።

3/ የጽሕፈት ቤቱ ኃላፊ የኮሚሽኑ ፀሐፊ ሆኖ ያገለግላል። https://chilot.me/2018/12/reconciliation-commission/

በአዋጁ እንደተመለከተው፣ በዚህ ሂደት ውስጥ የኮሚሽኑን አባላት ለመምርጥ የተቋቋመ (በይፋ የሚታወቅ) አካል አልነበረም። ተመራጮቹን " በጠቅላይ ሚኒስቴሩ አቅራቢነት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤቱ ይሰየማሉ " ከማለት ሌላ ለጠቅላይ ሚኒስቴሩ በእጩነት ማን እንደሚመርጣቸው በምን መመዘኛ አጣርቶ ለሀላፊነት እንደሚያጫቸው የሰፈረ ነገር የለም።

## የባለድርሻዎች ግብአት አለመኖር

አዋጁ የኮሚሽኑን አባላት አመራረጥ በተመለከተ በሂደቱ ላይ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ግብአት እንዲኖራቸው የደነገገም አይደለም። የሰብአዊ መብት ጥሰት ሰለባ የሆኑ ዜጎችም ሆኑ አጠቃላይ ዜጎች ድምጻቸውን ለማሰማት የሚያስችል አሰራር (ሜካኒዝም) ባዋጁ ውስጥ አልተካተተም።

አዋጁ ከሚለው ውጭ የተካሄደ ምክክርቢኖርእንኳበሚስጥርየተካሄደእንጂ ግልጽነት ያለው ነው ለማለት አይቻልም። ስለዚህም የኮሚሽኑ አመሰራረት ድክመት የሚጀምረው ከማቋቋሚያ አዋጁ ነበር ችግሩ ሲስተሚክ ነው ማለት ይቻላል። የኮሚሽኑን አባላት ምናልባት ጠቅላይ ሚኒስቴሩና አማካሪዎቻቸው ዝርዝር አዘጋጅተው ራሳቸው መርጠዋቸው ይሆናል። ይህ ታዲያ ለጠቅላይ ሚኒስቴር አብይ ያለን አክብሮት እንዳለ ሆኖ፣ የኮሚሽኑን ታአማኒነት ከፍ አያደርገውም። ጥንካሬም አይሰጠውም። ምናልባትም ጠቅላይ ሚኒስቴር አብይ የሚቀርቧቸውን የተወሰኑ ሰዎች ወይም የድርጅት ተወካዮች አማክረው ባገኙት ጥቆማ መሰረት የመጨረሻ ውሳኔ ሰጥተውም ሊሆን ይችላል። ይህም ቢሆን የኮሚሽኑን ገለልተኛነትና ታአማኒነት ከፍ የሚያደርገው በተለይም በተጎጅዎች እይታ የመተማመንን መሰረትን የሚገነባ አይደለም።

በሀገራችን ውስጥ ብሄራዊ እርቅ እውን መደረግ እንዳለበት አበክረው የሚያምኑ ክፍሎች ለረጅም ጊዜ ሰፊ ጥረት ሲያደርጉ ቆይተዋል፡፡ ከነዚህም ውስጥ በስብስብ ደረጃ፣ በክቡር ፊታውራሪ መኮንን ዶሪ የሚመራ ድርጅት እንዲሁም የ 25 ድርጅቶች ስብስብ የሆነው በሲያትል የተመሰረተው የፖለቲካ ድረጅቶች የብሄራዊ መግባባትና እርቅ ኮሚቴ፣ እንዲሁም "ትብብር" የተሰኘው የሲቪክ ማህበራት ስብስብ የሚጠቀሱ ናቸው።

እኔባለኝመረጃበዚህኮሚሽንአባላት ምርጫ ላይም ሆነ በኮሚሽኑ አወቃቀር ላይ ከላይ የጠቀስኳቸው ማናቸውም ቢሆኑ ስለተመሰረተው የብሄራዊ እርቅ ኮሚሽን ምንም አይነት ግብአት እንዲሰጡ አልተደረገም። ሀያ አምስቱ ድርጅቶች የመሰረቱት የብሄራዊ እርቅ ኮሚቴ፣ ቀደም ሲል ከፕሬዚደንት ሙላቱ ጋር ተገናኝቶ አላማውን እና ህልውናውን እንዳስታወቀ፣ በቀጣይም ለጠቅላይ ሚኒስቴር አብይ

ጽህፈት ቤትም ጊዜ ተሰጥቶት ሀሳቡን ለማቅረብ እድል እንዲሰጠው ቢያንስ ሁለት ደብዳቤ ጽፎ እንደነበረ፣ ባለፉት 10 ወራት ውስጥ በአዲስ አባባ ውስጥ በዚሁ የብሄራዊ እርቅ ጉዳይ ላይ ያተኮረ ቢያንስ ሶስት ትልልቅ የምክክር ስብሰባዎችን አንዳካሄደና ቢያንስ ባንዱ ስብሰባ ላይ የመንግስት ባለስልጣኖች (የለውጥ ሀይሉ) ተገኝተው እንደነበረ እኔ ራሴ የማውቀው ጉዳይ ነው።

እነዚህ በቅን መንፈስ ተነሳስተው በዚሁ አጀንዳ ላይ ሰፊ ስራ የሰሩ ክፍሎች በሂደቱ ላይ ግብአት እንዲሰጡ አለመደረጉ እምነትን ይቦረቡራል፤ አላስፈላጊ ጥርጣሬንም ይፈጥራል። ባጭሩ በኔ እይታ ምንም እንኳ በኮሚሽን አባልነት የተሰየሙትን አንዳንዶቹን በግል የማውቃቸውና በችሎታቸውም ሆነ ለፍትህ ባላቸው አቋም አይበገሬነት እጅግ የማከብረቸው ቢሆንም የኮሚሽኑ ምስረታ ነጻና ሁሉን አሳታፊ በሆነ አካል አለመካሄዱ፣ የተለያዩ ባለድርሻዎችን ግብአት ያካተተ አለመሆኑና አካሄዱ ግልጽነት የጎደለው መሆኑ ትልቅ ድክመት ነው እላለሁ።

ይህ ሂደት እጅግ ታላቅ ጥያቄ ውስጥ የሚገባው ደግሞ በኮሚሽኑ ውስጥ የተካተቱትን የተወሰኑትን በቅርበት ስንመለከት ነው፡፡ ከነዚህም ውስጥ ጥቂት ምሳሌወችን ላንሳ፡

## የኮሚሽኑ አባላት ቅንብር ጋር የተያያዙ ድክመቶች

የኮሚሽኑ አንዱ ተግባር በህወሀት መራሹ አገዛዝ ላላፉት 27 አመታት የተፈጸመውን የመብት ጥሰት መመርመር ነው እስከተባለ ድረስ እስከ ዶክተር አብይ ጠቅላይ ሚኒስቴር መሆን ድረስ የሀገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስቴር የነበሩት ጠቅላይ ሚኒስቴር ሀይለማርያም ደሳለኝ በዚህ ኮሚሽን ውስጥ መካተታቸው ፤ የኮሚሽኑን ታማኒነት በተለይም የሰባአዊ መብት ሰለባ በሆኑ ወገኖች በኩል እጅግ ዝቅ ያደርገዋል።

በጠቅላይ ሚኒስቴር ሀይለማርያም ዘመን ሀገራችን ኢትዮጵያ እጅግ መጠነ ሰፊና አሰከፊ የመብት ረገጣ የተካሄደባት ሀገር ነበረች። እርሳቸው ጠቅላይ ሚኒስቴር ከሆኑ በኋላ የተገደሉ፣ መዳረሻቸው የጠፉ፣ አካለ ስንኩላን የሆኑ የተገረፉ (ቶርች የተደረጉ) የተኮላሹ ፣ ግብረ ሰዶም የተፈጸመባቸው. ፣ በግዳጅ የወሲብ ጥቃት የደረሰባቸው ከህግ ውጭ ንብረታቸው የተነጠቀ፣ የተፈናቀሉ ወዘተ ኢትዮጵያውያን መጠነ ሰፊ ናቸው። ታዲያ የስርአቱ ግፍ ሰለባዎች እንዴት ነው ከእርሳቸው ፍትህን የሚያገኙት? በተካሄደው የመብት ረገጣስ እርሳቸው ተጠያቂ ሊሆኑ የማይችሉበት ሁኔታ ምንድን ነው?

አልፎ አልፎ እርሳቸው ለስም ብቻ ጠቅላይ ሚኒስቴር ተብለው የተቀመጡና ሁኔታውን ሁሉ ያሽከረክር የነበረው ህወሀት ነበር የሚለው አባባል በሰፊው ይስማል። ይህ እውነት ሊሆን ይችላል። ሆኖም ግን ይህ ጉዳይ በእርሳቸው በአቶ ሀይለማርያም አንደበት በእርቀሰላሙ ኮሚሽን ፊት መነገር የሚገባውና ለህዝብ በግልጥ መቅረብ የሚገባው አይደለምን?

ሂደቱ ከመጀመሩ በፊት ባንድ ድርጅት ውስጥ አንዱን ወንጀለኛ ሌላውን ነጻ ማድረግስ ፍትህን ተግባራዊ ከማድረግ ጋር እንዴት ይጣጣማል? ሁለቱ የቀድሞው ፕሬዚደንቶችም ጉዳይ በዚሁ ማእቀፍ ውስጥ የሚታይ ጉዳይ ነው። እዚህ ላይ ማናቸውንም ወንጀለኛ ናቸው ለማለት አይደለም። ሆኖም ግን በነሱ የስልጣን ዘመን የተካሄዱ የመብት ጥሰቶች በሚመረመሩበት በዚህ ሂደት ውስጥ እነርሱ መልሰው የእርቀሰላሙ ኮሚሽነሮች ሆነው መቅረባቸው ግራ የሚያጋባ ነው።

እርቀ ሰላሙ ከሰብአዊ መብት ጥሰት በተጨማሪ ሊመለከታቸው የሚገባው የተለያዩ ጉዳዮች ሊኖሩ እንደሚችሉና ለዚህም እነዚህ የቀድሞ ባለስልጣኖች ሊጫወቱት የሚችሉት ሚና እንደሚኖር አምናለሁ። ያ ግን በእርቀሰላሙ ኮሚሽን ውስጥ መግባትን የግድ አይልም። ሌላው ደግሞ የእርቀ ሰላሙ ስራ በሽዎች የሚቆጠሩ ወገኖቻችንን የቀጠፈው የደርግን አገዛዝን ዘመን ያደረሰውን ግፍ መመርመርን ያካትታል እስከተባለ ድረስ በዚያ ጊዜ በከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣን ያገለግሉ ግለሰቦችን በኮሚሽኑ አበልነት መሰየም ከላይ የጠቀስኩትን አይነት ትልልቅ ጥያቄን እንደሚያሰነሳ ግልጽ ነው። ምንም እንኳ ጉዟችን ወደእርቅና ይቅር መባባል እንደሆነ ግልጽ ቢሆንም፣ በዚያ ወቅት በከፍተኛ የመንግስት ሀላፊነት ተመድበው ያገለግሉ የነበሩ ግለሰቦች በኮሚሽኑ ውስጥ መካተታቸው የመብት ጥሰት ሰላባ ለሆኑ ሁሉ የሚያስተላልፈው መልእክት አወንታዊ አይሆንም ።




እነዚያ ሰለባዎች ከዚህ ኮሚቴ ይህ ነው የሚባል ፍትህን እናገኛለን ብለው በድፍረት በኮሚሽኑ ፊት ቀርበው ያለ አንዳች ፍራቻ የደረሰባቸውን በደል ሊገልጹ መቻላቸውም እጅግ አጠራጣሪ ነው። እንዚህ የቀድሞ ባለስልጣኖች ሀገራችንን ሊየገለግሉ የሚችሉባቸው እጅግ ብዙ ዘርፎች መኖራቸው ምንም አያጠራጥርም። የእርቀሰላም ኮሚቴ ግን ከነዚህ ውስጥ የሚመደብ አይሆንም። ሶስተኛው ደግሞ የኮሚሽኑ አባል የተደረጉትን የፖለቲካ ድርጅቶች ከፍተኛ መሪዎችን ይመለከታል።

ለኮሚሽን አባልነት የተመረጡት የፖለቲካ መሪዎች እጅግ የማከብራቸውና አንዳንዶቹም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ አብሬያቸው ሰፊ ስራን የሰራው ቢሆንም ባሁኑ ሳአት የፖለቲካ ድረጅት ከፍተኛ መሪዎች በዚህ ኮሚሽን ውስጥ እንዲገቡ መደረጉ ግን በእርቀሰላሙ ሂደት ከጥቅሙ ጉዳቱ የሚያመዝን ነው። እነዚህ ግለሰቦች የመብት ረገጣው ቀጥተኛ ሰለባዎች እንደሆኑ እየታወቀ እንዴት ነው መልሰው አስታራቂ የሚሆኑት። በሀገራችን ለማምጥት የምንሻው ፍትህንና ይቅርታን በዚህም ላይ ተመርኩዞ በጋራ መኳዝን ከሆነ እነዚህ ከፍተኛ የፖለቲካ መሪዎች እንዴት ነው ለሁሉም እኩል ፍትህን ያጎናጽፋሉ ተብሎ በተቃዋሚዎቻቸው ሊታመኑ የሚችሉት?

ይህ ሂደት ሂሳብ ማወራረድ ሳይሆን ተበደልኩ የሚሉትን ሁሉ የሚያደምጥ ይቅር መባባልን መሰረት ያደረገ ከሆነ እነዚህ የፖለቲካ መሪዎችስ ሊጠየቁባቸው የሚችሉ ጉዳዮች ሊኖሩ እንደሚችል እንዴት ይዘነጋል? ይህስ ከሆነ እነርሱ በሚመሯቸው ድርጅቶች ጉዳት ደርሶብናል የሚሉ የህብረተሰብ ክፍሎች በዚህ ኮሚሽን ላይ እንዴት ነው እምነት ሊኖራቸው የሚችለው? እነዚህ የተለያዩ ድክመቶች የኮሚሽኑን ታአማኒነት በተለያየ አቅጣጫ ጥያቄ ውስጥ ያስገቡታል። ሲያዩት ያላማረ ሲበሉት ያቅራል ነው እና ባስቸኳይ ሊታረሙም ይገባል።

## ጉድለቶቹን ለማረም ምን ይደረግ

በኔ እይታ የእርቀ ሰላሙ ሂደት መጀመር ለሀገራችን ያለው ጠቀሜታ እጅግ ከፍተኛ እንደመሆኑ መጠን ጅምሩ የሚታዩበትን ድክመቶች አስወግዶ ወደሚፈለገው ብሄራዊ እርቅና ሰላም ለመምጣት መደረግ አለባቸው የምላቸውን እንደሚከተለው አቀርባለሁ።

- የኮሚሽኑ አባላት ራሳቸውን በጽሞና መመዘንና ለዚህ ተግባር ትክክለኛው ሰው ነኝን በማለት ከራሳቸው ጋር በጥልቅ መወያየት ለኮሚሽኑ ውስጥ በመቆየታቸው ከብሄራዊ እርቅ ማሰፍን አንጻር የሚያበረክቱትን ጥቅምና ጉዳት ባግባቡ አመዛዝነውም ሀላፊነት

ወደ ገጽ 27 ዞሯል



# የጀርመን የጦር መሣሪያ ሽያጭ ቅሌት በየመን ጦርነት

የጀርመን ኩባንያዎች የጦር መሣሪያዎችን ለሳውድ አረቢያ እና ለተባበሩት አረብ ኤሜሬቶች የመሸጣቸው መረጃ እያነጋገረ ነው። DWን ጨምሮ በጀርመን እና በሌሎች የአውሮጳ ሃገራት ለሚገኙ መገናኛ ብዙኃን የሚሠሩ ጋዜጠኞች የተረባረቡበት የምርመራ ዘገባ ጀርመን ሠራሽ መሣሪያዎች በየመን ጦርነት መሳተፋቸውን ይዘረዝራል።

## የምርመራ ጋዜጠኝነት ዘገባ

በደቡባዊ የመን ግዛት አዋራማ ጎዳና ላይ አንድ ወታደራዊ አጀብ ይጓዛል። በገላጣው ተሽከርካሪ ላይ የሱዳን ወታዳራዊ የደንብ ልብስ የለበሱ ወታደሮች ተጭነዋል። አንዳንዶቹም በፈገግታ ተውጠው የድል ምልክት በጣታቸው ያሳያሉ። ጦር መሣሪያዎቻቸውንም ከፍ አድርገዋል። ሑቲ አማጺያንን ለመውጋት የመን ላይ የዘመተው የሳውድ አረቢያን ኃይል ለመደገፍ በባብ ኤል ማንዳብ የባሕር ወሽመጥ አድርገው ከሱዳን የመጡ ቅጥረኛ ወታደሮች ናቸው። ከጎርጎሪዮሳዊው 2015 ዓ.ም ጀምሮ ጦርነቱ

> “
>
> አልጀዚራ ቴሌቪዥን በጎርጎሪዮሳዊው 2017 ጥቅምት ወር ዘገባው ስለትሮ ቡና ታስተናግድ የነበረችው የየመኗ ሞካ ወደብ በሳውዲ መራሹ ጥምር ኃይል ቁጥጥር ሥር መቆየቷን አመልክቷል።

የመን ውስጥ በሺህዎች የሚገመቱ ሲቪሎችን ሕይወት ቀጥፏል። የተባበሩት መንግስታት ድርጅት (ተ.መ.ድ.) በዘመኑ ከፍተኛ ሰብአዊ ቀውስ የታየው የመን ውስጥ መሆኑን ያመለክታል። በሀገሪቱ በሚሊየን የሚገመቱ በተለይ ሕጻናት ለጠኔ ተዳርገዋል።

## ጀርመን ሠራሽ ጦር መሣሪያዎች

በጎርጎርጎሪዮሳዊው 2015 የአሶሲየትድ ፕረስ ዘጋቢ ከየመኗ የወደብ ከተማ አደን ላይ የቀረፀው ፊልም ያሳየው የሱዳን ቅጥረኛ ወታደሮችን ብቻ አልነበረም። ንብረትነታቸው የተባበረው አረብ ኤሜሬቶች የሆኑ ታንኮችንም ጭምር እንጂ። ታንኮቹ ዩናይትድ ስቴትስ እና ጀርመን ሠራሽ ናቸው። የጀርመኑ የመከላከያ መሣሪያ ፋብሪካ ዱዩናሚት ኖቤል የ81 ሚሊኒየን ዩሮ ምርቱን የመን ውስጥ የእግረኛ ጦር የሚሰነዘረውን ጥቃት ለምትመራው ኤሜሬትስ የመላክ ፈቃዱን ከፌደራል መንግሥቱ ያገኘው የዛሬ 10 ዓመት ነው።

«የጀርመን የጦር መሣሪያ በየመን ጦርነት ውስጥ ገብቷል ወይ?» በሚል DW በሙኒኩ የፀጥታ ጉባኤ ላይ ጥያቄ

> “ የፌደራል ጀርመን ተጣማሪ መንግሥት በየመን ጦርነት ለሚሳተፉ ሃገራት የጦር መሣሪያ እንዳይሸጥ ቢደነግጉም የሳውዲው ጋዜጠኛ ጀማል ኻሾግጂ ኢስታንቡል ውስጥ እስከተገደለበት ጊዜል ድረስ ውሳኔው ተግባራዊ እንዳልሆነ መገናኛ ብዙኃን ዘግበዋል፡፡

ያቀረበላቸው የጀርመን የኤኮኖሚ ሚኒስትር ፒተር አልትማየር ፤

«የማውቀው ነገር የለም፤ በጥምር መንግሥታችን በቀጥታ እና ወዲያው በየመን ግጭት ውስጥ ጣልቃ ለገቡ ወገኖች ወታደራዊ መሣሪያዎች እንዳይሸጡ እጅግ ገዳቢ መመሪያዎችን አውጥተናል። ይህ ተግባራዊ እየሆነ ነው፤ እሱን በተመለከተ አዲስ ነገር አልሰማሁም።» ነው ያሉት።

ሆኖም ግን እነዚህ እንደሳውድ አረቢ እና ኤሜሬትስ ያሉት ሃገራት ከጎርጎሪዮሳዊው 2015ዓ,ም ጀምሮ የጀርመንን የጦር መሣሪያዎች ሲሸምቱ ነበር። የኤኮኖሚ ሚኒስትሩ ግን መሣሪያዎቹ ለጦርነት እንደሚውሉ አለማወቃቸውን ለማስረዳት ሞክረዋል። ሆኖም ግን የጀርመን የጦር መሣሪያ አምራች ኩባንያ ምርቶች ፎቶግራፎች እና የቪዲዮ ምስሎች በኢንተርኔት ማለትም በትዊተር፤ በዩቲዩብ እና በጉግል ኽርዝ ይገኛሉ። የጀርመን ጦር መሣሪያዎች ላይ ምርመራ ያካሄዱ ተንታኞች ጦር መሣሪያዎቹ በየመኑ ጦርነት በምድር፣ በአየር እና በባሕር መሳተፋቸውን የሚያሳዩ በርከት ያሉ መረጃዎችን አግኝተዋል።

## አሰብ፤ ለየመኑ ጦርነት ተልእኮ መንደርደሪያ

ሌላው የኤርትራዋ አሰብ ወደብ ለየመኑ ጦርነት የዘመቻ ጣቢያ ሆናለች። በየመን እና በአሰብ ወደብ መካከል ያለው ርቀት 60 ኪሎ ሜትር ብቻ ነው። ከዚህ ስፍራ የሚነሱት የአረብ ኤሜሬቶች የጦር መርከቦች ወደ አደን ወደብ በቀላሉ ፈጥነው መድረስ ይችላሉ። ቅጥረኛ ወታደሮችም በዚሁ ወደብ አማካኝነት ወደ የመን እንዲገቡ በኤሜሬቶች እና በኤርትራ መካከል ስምምነት መደረጉንም የተመድ አመልክቷል። ድርጅቱ በጎርጎሪዮሳዊው 2009 ዓ,ም በኤርትራው ፈላጭ ቆራጭ መንግሥት ላይ የጣለውን የመሣሪያ ማዕቀብ ጥሷል ሲልም ይተቻል። ለእገዳው ቁብ ያልሰጠችው ኤሜሬትስ ጀርመን ሠራሽ የጦር መርከቦቿን በአሰብ ወደብ ላይ ማንሳፈፏን የሳተላይት ፎቶዎች ያሳያሉ። ሮኬት የተጠመደባቸው የጦር መርከቦች ብሬመን በሚገኝ የጀርመን ኩባንያ የተሠሩ እና 65 ሜትር ርዝመት ያላቸው ናቸው።

አልጃዚራ ቴሌቪዥን በጎርጎሪዮሳዊው 2017 ጥቅምት ወር ዘገባው ለወትሮ ቡና ታስተናግድ የነበረችው የየመኗ ሞካ ወደብ በሳውዲ መራሹ ጥምር ኃይል ቁጥጥር ሥር መቆየቷን አመልክቷል። በዚህ ወቅትም የጀርመን ብቻ ሳይሆኑ የተለያዩ አውሮጳ ሃገራት የጦር መሣሪያዎችም ለዚሁ ተግባር ውለዋል። ለአብነትም ሳውዲ የተጠቀመችበት እና በያዝነው ዓመት ጥር ወር ላይ የመን ውስጥ የተከሰከሰው ቶርኔዶ ተዋጊ ጀትን ይጠቀሳል። የተዋጊ ጀት ነዳጅ ይሞሉ የነበሩ የኤርበስ ምርቶችም እንዲሁ ጀርመን ሠራሽ አካላት የተገጠሙላቸው አውሮፕላኖች መሆናቸውንም ምርመራው አሳይቷል። እንዲህ ያሉ ምርቶች ለጦርነት በመዋላቸው ጀርመን በቀጥታ በጦር መሣሪያ ንግዱ ተሳትፋለች ማለት አይቻልም በሚል የሚከራከሩ አሉ። በሌላ በኩል ደግሞ ጀርመን ስልታዊ ተጓዳኝ አድርጋ ከምትወስዳቸው ሳውዲ እና አረብ ኤሜሬቶች ጋር መናገዷ በቀጥታ በየመን ጦርነት እጇን እንደከተተች ያስመስላታል በሚልም የሚተቹ አልጠፉም።

የፌደራል ጀርመን ተጣማሪ መንግሥት በየመን ጦርነት ለሚሳተፉ ሃገራት የጦር መሣሪያ እንዳይሸጥ ቢደነግጉም የሳውዲው ጋዜጠኛ ጀማል ኻሾግጂ ኢስታንቡል ውስጥ እስከተገደለበት ጊዜል ድረስ ውሳኔው ተግባራዊ እንዳልሆነ መገናኛ ብዙኃን ዘግበዋል። ይህ እገዳም ቢሆን የፊታችን መጋቢት መጀመሪያ ቀናት ላይ ያበቃል። ይህ በእንዲህ እንዳለም ከኤሜሬቶች ጋር ካለፈው ጥቅምት እስከ ታኅሳስ ወር በተደረገው ስምምነት ከ40 ሚሊየን ዩሮ በላይ የሚያወጣ የባሕር ኃይል መከላከያን የሚጨምረው የጦር መሳሪያ ሽያጭ ውል አሁንም አልተቋጨም። የመናዊቱ ጋዜጠኛ እና የሰላም ኖቤል ተሸላሚ ታዋኮል ካርማን ጀርመን ለሳውዲ እና ለኤሜሬትስ መሣሪያ መሸጥ እንድታቆም ጥሪ አቅርባለች።





# ‹የማይታየው ገዳይ› እና የዓለማችን እጣ ፈንታ

“

**የኤዥያ የኢኮኖሚ ኃያሏ ቻይና በበኩሏ ከሃምሳ እጅግ የተበከሉ የዓለማችን ከተሞች መካከል ሃያ ሁለቱን የያዘች ሲሆን ዋና ከተማዋ ቢይጂንግ በ2017 የነበረችበትን ሁኔታ ዘንድሮ ማሻሻሏ ተነግሯል፡፡ የውጤቱ ምክንያትም ከፍተኛ የቁጥጥር ሥርዓት መዘርጋቱና ስኬታማ የአየር ብክለት ቅነሳ ፖሊሲዎች ተግባር ላይ መዋላቸው ነው**

በቅርቡ የወጣ የአየር ንብረት ለውጥ መረጃ በከባድ የአየር ብክለት ከሚታወቁ ሀገራት መካከል ሕንድ ቀዳሚውን ደረጃ መያዟን አመልክቷል፡፡ በአስከፊ ሁኔታ አየራቸው ከተበከለ የዓለማችን ከተሞች መካከል አሥሩ የሚገኙት በሕንድ መሆኑንም ነው የጠቆመው፡፡ የሀገሪቱ ዋና ከተማ ከሆነችው ኒው ዴልሒ በ30 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የምትገኘው ጉሩግራም የተሠኘች ከተማ በ2018 ዓ.ም እጅግ አሳሳቢ የአየር ብክለት ካስተናገዱ የዓለማችን ከተሞች ግንባር ቀደሟ ሆናለች፡፡ ፋይሳላባድ የተባለችውን የፓኪስታን ከተማ ጨምሮ ሌሎች ሦስት የሕንድ ከተሞች የአየር ብክለት ደረጃውን የሚመሩ አምስት ከተሞች ሆነዋል፡፡ በመረጃው መሠረት ክፉኛ አየራቸው ከተበከለ ሃያ የዓለም ከተሞች መካከል አሥራ ስምንቱ በሕንድ ሲገኙ ሁለቱ ደግሞ በፓኪስታንና በባንግላዲሽ ነው የሚገኙት፡፡

## ሕንድ

ከሃያ ሚሊየን ሕዝብ በላይ የሚኖርባት ዋና ከተማዋ ኒው ዴልሒ በዓለም 11ኛ ደረጃን ስትይዝ እርሷን ተከትለው አስከፊውን ብክለት የተያያዙት ደግሞ የባንግላዲሸዋ ዳካ እና የአፍጋኒስታኗ ካቡል ሌሎች ዋና ከተሞች ናቸው፡፡

‹‹የአየር ብክለት ሕይወታችንንና ነጋችንን ሠርቆናል›› ይላሉ የግሪን ፒስ ደቡብ ምሥራቅ ኤዥያ ዋና ሥራ አስኪያጁ ዬብ ሳኖ፡፡ ይቀጥሉናም ‹‹በአየር ብክለት ምክንያት ካጣናቸው የሰው ልጆች በተጨማሪ 225 ቢሊየን ዶላር የሚገመት የሠራተኛ አቅም አጥተናል፤ በትሪሊየን የሚቆጠር ገንዘብም ለሕክምና ወጪ ሆኗል›› በማለት ያስረዳሉ፡፡ ይህን መረጃ የምንፈልገው ስለምንተነፍሰው አየር ሰዎች እንዲያስቡ ለማድረግ ነው የሚሉት ዋና ሥራ አስኪያጁ ጥራት ያለው አየር በሕይወታችን ውስጥ ያለውን አዎንታዊ ተፅዕኖ ማወቅ ከቻልን በጣም አስፈላጊ ለሆነው ነገር የተግባር ምላሽ ለመስጠት እንነሳለን የሚል መልእክትም አስተላልፈዋል፡፡

ኤርቪዠዋል ኤንድ ግሪን ፒስ ኢንዴክስ የተባለው የጥናት ውጤት 92 የዓለማችን ከተሞች ጤናማ ያልሆነ አየር እያስተናገዱ እንደሚገኙ ጠቁሟል፡፡ ይህም በሳንባ ጤና ላይና በደም ዝውውር ሥርዓት ላይ ከፍተኛ መስተጓጎል በማስከተል በለጋ ዕድሜ ለሞት ሊዳርግ እንደሚችል ነው ያስገነዘበው፡፡

የዓለም የጤና ድርጅት በበኩሉ



በየዓመቱ ሠባት ሚሊየን ሰዎች በአየር መበከል ምክንያት ሕይወታቸውን እንደሚያጡ ጠቁሟል፡፡ ያልተስተካከለ የልብ ምት፣ ከፍተኛ የአስም ህመም፣ የሳንባ ሥራውን መቀነስም በአየር መበከል ምክንያት የሚመጡ ሌሎች አሳሳቢ ችግሮች ናቸው፡፡

ሎሪ ማይሊቪርታ የተባሉት የግሪንፒስ ዓለማቀፍ አየር ብክለት ቁጥጥር ከፍተኛ ተንታኝ ለአየር ብክለት የሚዳርጉ በርካታ ምክንያቶች መኖራቸውን አስታውቀው ዋነኞቹ ከቤት ውስጥ የሚወጡና የኢንዱስትሪ ልቀቶች ናቸው ብለዋል፡፡ የትራንስፖርት መገልገያዎችን ከፍተኛ አስተዋጽኦም አልዘነጉም፡፡

1.3 ቢሊየን ሕዝብ ባላት የደቡብ ኤዥያዋ ሀገር በአሁኑ ወቅት እየታየ ያለው የአየር ብክለት ከሀገሪቱ አስተዳዳሪዎች ፈጣን ምላሽ የሚያስፈልገው መሆኑን የዘርፉ ባለሙያዎች ያስረዳሉ፡፡ «እስካሁን ተቋቁመነዋል፤ ነገር ግን ሰውነታችን በጣም እየተጎዳ ነው፡፡ የመንግሥት አካላትም ችግሩን ሳይሆን ወቀሳውን ነው ለመቅረፍ እየሞከሩ ያሉት» የሚሉት የ‹ኬር ፎር ኤር ኢንዲያ› ግብረ ሰናይ ድርጅት መሥራችና ፕሬዚዳንቷ ጃዮቲ ፓንዴ ላቫካሬ ናቸው፡ ፡ በእንዲህ ዓይነት ጥራት የሌለው አየር ውስጥ መኖር እጅግ አስፈሪ መሆኑንም ነው የገለጹት፡፡

በጠቅላይ ሚኒስትር ናሬንድራ ሞዲ የምትመራው ሕንድ በሚሊየን የሚቆጠሩ ዜጎቿን ከድህነት ለማውጣት የሥራ ዕድል መፍጠር የሚያስችል የኢኮኖሚ ዕድገት ላይ ነው ትኩረቷን ያደረገችው፡፡ የፖለቲካና የአየር ንብረት ጉዳይ ተንታኞች የሞዲ መንግሥት የአየር ብክለትን ጨምሮ ለአካባቢ ጥበቃ ተግባራት በቂ ትኩረት አለመስጠቱን ይገልጻሉ፡፡ «በብሔራዊ ደረጃ ዓመቱን ሙሉ የሚሠራ ሥራ ያስፈልገናል፡፡ በሞተር ለሚጠቀሙ መጓጓዣዎች ቆሻሻ ነዳጆችን በማስወገድ ንፁህ ነዳጆች መጠቀም፣ በሕዝብ አደባባዮች ቆሻሻ የማቃጠል ተግባራትን ማስቆምና ከኢንዱስትሪዎች የሚወጡ ልቀቶችን መቀነስ አስፈላጊ ነው» ይላሉ ፕሬዚዳንቷ፡፡

## ቻይና

የኤዥያ የኢኮኖሚ ኃያሏ ቻይና በበኩሏ ከሃምሳ እጅግ የተበከሉ የዓለማችን ከተሞች መካከል ሃያ ሁለቱን የያዘች ሲሆን ዋና ከተማዋ ቤይጂንግ በ2017 የነበረችበትን ሁኔታ ዘንድሮ ማሻሻሏ ተነግሯል፡፡ የውጤቱ ምክንያትም ከፍተኛ የቁጥጥር ሥርዓት መዘርጋቱና ስኬታማ የአየር ብክለት ቅነሳ ፖሊሲዎች ተግባር ላይ መዋላቸው ነው ተብሏል፡፡

> **የማይታየው ገዳይ በመባል የሚጠራው የአየር ብክለት ችግር 25 በመቶ ለሚሆኑት የልብ ችግሮች ምክንያት እንደሚሆን ይነገራል፡፡ በዓለማቀፍ ደረጃ በየዓመቱ በስትሮክ ምክንያት ለሚፈጠር የ1.8 ሚሊዮን ሰዎች ሞትም መነሻ ይሆናል፡ ፡ 43 በመቶ የሚሆኑት በሳንባ ህመምና በሳንባ ካንሠር ለሚፈጠሩ ሞቶች የራሱን አስተዋፅኦ ያበረክታል፡፡ በየዓመቱም በሳንባና በካንሠር ምክንያት 1.8 ሚሊዮን የዓለማችን ሰዎች እንዲሞቱ ያደርጋል፡፡**

በፕሬዚዳንት ዢ ጂንፒንግ የሚመራው የቻይና ኮሙኒስት ፓርቲ የሀገሪቱ መሠረታዊ ችግር በሆነው የአየር፣ የውሃና የመሬት ብክለት ላይ ጦርነት አውጆ መንቀሳቀስ ከጀመረ ሰነባብቷል፡፡ የቻይና ውጤታማነትም ሀገራት የአየር ንብረት ለውጥ ላይ ቅድሚያ ሰጥተው መሥራት ከቻሉ ዓለማችን ላይ የተደቀነውን ስጋት መቅረፍ እንደሚቻል ያሳያል ይላሉ የዘርፉ አጥኚዎች፡፡

በከፍተኛ ሁኔታ ከተበከሉት አሥሩ የዓለማችን ሀገራት መካከል ሰባቱ በሕንድ የሚገኙ ሲሆን ሁለቱ በፓኪስታን፣ አንዱ ደግሞ በቻይና ይገኛሉ፡፡ የሕንዷ ጉሩግራምና ጋዚአባድ የመጀመርያና ሁለተኛውን ደረጃ ሲይዙ የፓኪስታኗ ፋይዛላባድ ሦስተኛ ደረጃ ላይ ተቀምጣለች፡፡ ፋሪዳባድና ብሒዋዲ አራተኛና አምስተኛ ላይ የተቀመጡ ሌሎች የሕንድ ከተሞች ናቸው፡፡ ኖይዳ፣ ፓትና፣ ሆታን፣ ሉክናው እና ላሆር እስከ አሥር ከተዘረዘሩት በአየር ብክለት የሚሰቃዩ የዓለማችን ከተሞች መካከል በቅደም ተከተል ተቀምጠዋል፡፡

## ቁጥሮች ምን ይላሉ?

በዓለማችን በየዓመቱ 7 ሚሊየን ሰዎች በአየር ብክለት ለሞት ይዳረጋሉ፡፡ ከአሥሩ የዓለማችን ሰዎች ዘጠኙ የሚተነፍሱት በከፍተኛ መጠን በካይ የሆነ አየርን ነው፡፡ ይህ አየር ለስትሮክ፣ ለልብ ህመም፣ ለሳንባ ካንሠር፣ ለሳንባ ምችና ለመተንፈሻ አካላት ኢንፌክሽኖች ጉዳት የሚዳርግ ነው፡፡ የማይታየው ገዳይ በመባል የሚጠራው የአየር ብክለት ችግር 25 በመቶ ለሚሆኑት የልብ ችግሮች ምክንያት እንደሚሆን ይነገራል፡፡ በዓለማቀፍ ደረጃ በየዓመቱ በስትሮክ ምክንያት ለሚፈጠር የ1.8 ሚሊየን ሰዎች ሞትም መነሻ ይሆናል፡፡ 43 በመቶ የሚሆኑት በሳንባ ህመምና በሳንባ ካንሠር ለሚፈጠሩ ሞቶች የራሱን አስተዋፅኦ ያበረክታል፡፡ በየዓመቱም በሳንባና በካንሠር ምክንያት 1.8 ሚሊየን የዓለማችን ሰዎች እንዲሞቱ ያደርጋል፡፡

በከተማ ከሚኖረው የዓለማችን ሕዝብ መካከል 91 በመቶ የሚሆኑት የዓለም ጤና ድርጅት ካስቀመጠው የአየር ልቀት መጠን በላይ የሆነ አጠቃቀም በሚኖርባቸው ከተሞች የሚገኙ ናቸው፡፡



# በመጨረሻም ...

ከገጽ 6 የዞረ

ሊሳካም ላይሳካም ይችላል የሚሉት ምሁራኑ ለውህደት ከሚደረገው እንቅስቃሴ ጎን ለጎን ግንባሩ እና አጋሮቹ መቶ በመቶ የተቆጣጠሩትን የፓርላማ ሥርዓትም ማሻሻል እንደሚገባም አመልክተዋል።

በፖለቲካ ቀውስ እና አለመረጋጋት የሚናጠው ገዥው ፓርቲ ኢህአዲግ ከአመታት በፊት ወጥኜው ነበር ባለው ወደ ተዋሃደ አንድ ፓርቲ የመሸጋገር ዕቅድ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ የሰጠው ባለፈው ነሐሴ ወር ላይ በሀዋሳ በተካሄደው ጉባኤ ነበር።

## አዲሱ የኢህአዴግ መንገድ ወዴት?

ኢትዮጵያ ኅብረ ብሔር አገር መሆኗን በተደጋጋሚ የሚጠቅሰው ኢህአዲግ በመተዳደሪያ ደንቡም ይሁን በሚመራባቸው አጠቃላይ የአደረጃጀት መርሆዎች የግንባሩን ዓላማ ለማሳካት ብሔረሰባዊ አደረጃጀቶች ብቻ አዋጭ መሆናቸውን ነው ደጋግሞ የሚገልጸው። ግለሰቦችን በተናጥል የሚያሰባስብ ኅብረ ብሔር ድርጅት ግን ሕገ መንግሥታዊ ዋስትናን ለማረጋገጥ እና ብሔር ብሔረሰቦችን እና ሕዝቦችን ለማታገል አቅም አይኖረውም የሚል ዕምነት አለው። ይህን እምነቱን ንዶ ወደአንድ ሀገራዊ ፓርቲ ራሱን ለመቀየር መወሰኑ ብዙዎችን አስገርሟል፡፡

ይህ ውሳኔ ለ 27 ዓመታት በዘለቀው የግንባሩ አመራር መጻኢ ዕድልም ሆነ በአገሪቱ የወደፊት ጉዞ ላይ ምን ሊፈጠር እንደሚችል ከወዲሁ መተንበይ እንዳማይቻል ብዙዎች ይስማማሉ።

‹‹ሀገራዊ አንድነት ለሁለንተናዊ ብልፅግና›› በሚል መሪ ቃል በሀዋሳ ለሶስት ቀናት በተካሄደው የኢህአዴግ 11ኛ ጉባኤ ላይ የኢህአዴግ ሊቀመንበር ዶ/ር ዐቢይ አህመድ ጉዳዩን አስመለክቶ በሰጡት አስተያየት ኢህአዴግ የሁሉም ህዝቦች ፓርቲ እንዲሆን የተቀመጠው አቅጣጫ በአገራዊ አለመረጋጋቱ ምክንያት ጥናቱ ተጠናቆ ባይደርስም ፣ የክልል አጋር ፓርቲዎች የኢህአዴግ አካል መሆን እንዲችሉ የሚደረግበት ወቅት አሁን መሆኑን አመልክተው ነበር፡፡

የዓመታት ፈተና

እንደሚታወቀው ኢሕአዴግ የአራት ክልሎች እና የፌዴራል መንግሥቱ ገዢ ፓርቲ ነው። የሌሎቹ አምስት ክልሎች ገዢ ፓርቲዎችን ‘አጋር’ በሚል ይጠራቸዋል። በምርጫ ቦርድ አሠራር ‘አጋር’ አደረጃጀት ስለሌለ ቦርዱ እንደተለያዩ ፓርቲዎች ነው የሚመለከታቸው። ‘አጋር ድርጅቶቹ’ ጋር ኢሕአዴግ ያለው ግንኙነት ግን በምርጫ ቦርድ ያልተመዘገበ፣ ደንቡም ግልጽ ያልሆነ ነው። የሚታወቅ የጋራ የሥራ አስፈፃሚ የላቸውም። ይህ ጉዳይ ኢሕአዴግ የእነዚህን አምስት ክልላዊ መንግሥታት “ሁኑ እንዳላቸው ብቻ የሚሆኑ አሻንጉሊቶች ናቸው” ለሚለው ሕዝባዊ ጥርጣሬ ማረጋገጫ ሆኖ ዓመታትን ዘልቋል ይላል ወጣቱ አክቲቪስት በፍቃዱ ኃይሉ በአንድ ጽሑፉ፡፡ ምክንያቱን ሲያስቅምጥም ‘አጋር ድርጅቶቹ’ ከኢሕአዴግ ያፈነገጠ ውሳኔ አሳልፈው አለማወቃቸውን ይጠቅሳል፡፡

ፕሬዚዳንት አብዲ ኢሌይ በቁጥጥር ስር ውለው ወደወህኒ ከመወርወራቸው አስቀድሞ በኢትዮጵያ ሶማሊ ክልል የተፈጠረው ችግር እና የፌዴራል መንግሥቱ ሊቆጣጠረው መቸገሩ የዚህ አዛዥ-ታዛዥነት ዘመን ሊያበቃ እንደሚችል አመላካች ሆኖ አልፏል።

የሶማሊ ክልል የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት ከፀደቀ ወዲህ ባሉት 23 ዓመታት ውስጥ አሁን በጊዜያዊነት የተቀመጡትን ክልላዊ ፕሬዚደንት ሳይጨምር፥ 10 ፕሬዚደንቶችን አፈራርቋል። ከፕሬዚደንት አብዲ ሞሐመድ ዑመር (አብዲ ኢሌይ) በስተቀር ቀደሚዎቹ ዘጠኝ ፕሬዚደንቶች መካከል ከ3 ዓመት በላይ ሥልጣን ላይ ለአንድ ሙሉ የምርጫ ጊዜ ያገለገለ ፕሬዚደንት በክልሉ አልነበረም። ፕሬዚደንት አብዲ ኢሌይ ግን ለ8 ዓመታት ሥልጣን ላይ በመቆየት የክልሉን ሪከርድ ሰብረዋል። የክልሉ አመራሮች ሥልጣን ላይ የማይቆዩት በፖለቲካዊ አለመረጋጋት ጦስ ነው።

ከዚህ አለመረጋጋት በመነሳት የፕሬዚደንት አብዲ ኢሌይ ይህን ያክል ሥልጣን ጨብጦ መቆየት መቻል አስገራሚ ሊሆን ይችላል። ፕሬዚደንት አብዲ ኢሌይ ወደ ሥልጣነ መንበሩ ከመምጣታቸው በፊት፥ በወቅቱ በሽብርተኝነት የተፈረጀውን የኦጋዴን ብሔራዊ ነጻነት ግንባር (ኦብነግ) ሠራዊትን ከኦጋዴን ጠራርጎ ለማስወጣት የተቋቋመውን ‘ልዩ ፖሊስ’ መርተዋል። ፕሬዚደንት አብዲ ኢሌይ የክልሉን ሥልጣን ከተቆጣጠሩ በኋላም ቢሆን ‘ልዩ ፖሊስ’ በክልሉ የሚንቀሳቀስ ትልቁ የታጠቀ ኃይል ሆኖ ከመቀጠሉም ባሻገር፥ ከፍተኛ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶችን በማደረስ ሥሙ ይነሳል። ከሁሉም በላይ ግን

የፕሬዚደንቱን ሥልጣን ለማስጠበቅ መሣሪያ ሆኗል በመባል ደጋግሞ ይወቀሳል።

የሶማሊ ክልል ነዳጅ የተገኘበት መሆኑ የክልሉን ሀብት አስጠብቃለሁ በሚለው አጋዴን እና በፌዴራል መንግሥቱ መካከል ዘላቂ ውጥረት ፈጥሯል። ይህም ላለፉት ፖለቲካዊ አለመረጋጋቶች መንስዔ ነበር። በፕሬዚደንት አብዲ ኢሌይ ይመራ የነበረው የሶማሌ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (ሶሕዴፓ) ከፌዴራል መንግሥቱ ጋር እጅ እና ጓንት ሆኖ በመሥራት ክልሉ ውስጥ ያለውን ተቃውሞ በኃይል በመቆጣጠር ለክልሉ ጊዜያዊ መረጋጋት አስገኝቶ ነበር። ምንም እንኳን ክልሉ "የኮንትሮባንድ ንግድ መነኻሪያ ሆነ" የሚል አቤቱታ በተደጋጋሚ ቢሰማም፥ ኢትዮጵያ ከአል ሻባብ ጋር በምታደርገው ውጊያ ክልሉ ወሳኝ ጂኦግራፊያዊ ፋይዳ ነበረው። ስለዚህም የፌዴራል መንግሥቱ የክልሉን መንግሥት ጥፋቶች በዝምታ ሲያልፍ ነበር። እንዲያም ሆኖ በፌዴራሉ መንግሥት ውስጥ የነበረው ፖለቲካዊ ውክልና እዚህ ግባ የሚባል አልነበረም።

## የአጋር ፓርቲዎች እጣ ፋንታ

ቀጣይ የኢሕአዴግ 'አጋር' ፓርቲዎች ሁለት አማራጮች እጃቸው ይላል በፍቃዱ ኃይሉ። ከኢሕአዴግ አባል ፓርቲዎች መርጠው ለአንዱ በመወገን ሌላኛው ላይ የፖለቲካ ብልጫ ማሳየት፤ አልያም ነጻነታቸውን አስከብረው በራሳቸው መወሰን። ይሁን እንጂ፣ እነዚህ የኢሕአዴግ 'አጋር' ፓርቲዎች የሚገዟቸው ክልሎች የሕዝብ ቁጥራቸው እንዲሁም የፖለቲካ ልኂቃኖቻቸው ቁጥር አነስተኛ በመሆኑ በተናጠል ፌዴራል መንግሥቱ ውስጥ የሚኖራቸው ተፅዕኖ ደካማ ነው። ይህንን አስቀድሞ የተረዳ የሚመስለው እና በኦሕዴድና ብአዴን ትብብር ተገፍቻለሁ የሚል ቅሬታ ያለው ሕወሓት፥ ከነዚህ የኢሕአዴግ 'አጋር' ድርጅቶች ጋር በመተባበር የተወሰነ ተፅዕኖ ለመፍጠር ይሞክር ይሆናል ሲልም ይጠቅሳል።

መቼ ይመሰረታል?

የዘጠኙንም ክልል ፓርቲዎችን ያካተተ ሀገር አቀፍ ፓርቲ ለመመስረት የተወሰነው ውሳኔ በ11ኛው የኢሕአዴግ ጉባኤ ላይ በተቀመጠው አቅጣጫ መሰረት እየተጓዘ መሆኑን የኢህአዴግ ጽህፈት ቤት ሃላፊ አቶ ብናልፍ አንዱአለም ከሰሞኑ ገልጸዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር አብይ አህመድ በበኩላቸው ከጥቂት ወራት በኋላ የአፋር፣ የቤንሻንጉል ጉምዝ፣ የሶማሌ፣ የኦሮሞ፣ የአማራ ፓርቲ የሚባል ነገር የለም ማለታቸው የሚታወስ ሲሆን አቶ ብናልፍ እንዳሉት ውሳኔው ሁሉም ዜጎች በእኩልነት በብቃታቸው እንዲሳተፉ እድል የሚፈጥር ነው።

## ለሌሎች ፓርቲዎች ምን ይነግራል?

ኢህአዴግ አጋሬ የሚላቸው ከሶማሌ፣ ከአፋር፣ ከቤንሻንጉል፣ ከጋምቤላና ከሐረሪ ክልሎች ለተውጣጡ አካላት የነገረው ይህ የለውጡ አሳቤ ኢህአዴግ ውህደቱ በውስጡ ብቻውን ሳይሆን አጋር ፓርቲዎችን ጨምሮ ለመዋሀድ ከፍተኛ ፍላጎት እንዳለው ያረጋገጠ ነው ይላሉ ምሁራን፡፡

እንደሚታወሰው ግንባሩ በ11ኛ ጉባዔው ማጠናቀቂያ ላይ ባወጣው የአቋም መግለጫ ለአጋር ፓርቲዎቹ ተመሳሳይ አቋሙን እንዲህ ሲል ገልጾም ነበር፡ ፡ "በጉባኤያችን መክፈቻ ስነ – ስርዓት ላይ እንዳስተላለፋችሁት መልዕክት ሁሉ ኢህአዴግም ከእናንተ ጋር በመዋሀድ አንድ ሀገራዊ ፓርቲ በመሆን ሁሉም ኢትዮጵያውያን የሚሳተፉበት እና የሚታገሉበት የጋራ መድረክ ይሆን ዘንድ የጥናት ሥራዎችን ተጀምረዋል፡፡ በመሆኑም እንደ አንድ ህብረ ብሄራዊና ሀገራዊ ድርጅት ለመንቀሳቀስ በሚያስችለን ህሊናዊና ነባራዊ ሁኔታ ላይ መሆናችንን እየገለጽን ለዚህ ዓላማ ስኬት ሁላችንም የበኩላችንን ድርሻ እንድንወጣ በዚህ አጋጣሚ ጥሪያችንን እናስተላልፋለን"

ይህ የኢሕአዴግ እንቅስቃሴ በብሔር ስም እየተደራጁ ለሚገኙትና ለተደራጁት ፓርቲዎች ምን መልዕክት ያስተላልፍ ይሆን የብዙዎች ጥያቄ ሆኗል፡፡

ከ70 በላይ የፖለቲካ ፓርቲዎች ኢትዮጵያ ውስጥ ይንቀሳቀሳሉ፡፡ አብዛኞቹ በብሄር ስም የተደራጁ ናቸው፡፡ እነዚህ ፓርቲዎች በተለይ ደግሞ ተቀራራቢ የፖለቲካ ዓላማ ያላቸው በአንድ ላይ በመሰባሰብ ወደ ሦስት ወይም አራት ዝቅ ቢሉ የበለጠ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለማጠናከር ጠቃሚ እንደሆነ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ማንሳታቸው ይታወሳል፡፡ ህዝብንና ሀገርን ተጠቃሚ እንደሚያደርግም አመልክተዋል፡፡

የፖለቲካ ፓርቲ መሪዎችም ጠቅላይ ሚኒስትሩ ያቀረቡትን ምክረ ሀሳብ እንደሚደግፉት በመግለጽ ከዚህ ቀደም ባለመሰባሰባቸው ያጡትን ዕድሎች፤ ቢሰባሰቡ ሊያገኙ ስለሚችሉት ጥቅም፤ ለመሰባሰብ ስላለው አስቻይ ሁኔታና ተግዳሮት አስተያየታቸውን መስጠታቸው አይዘነጋም፡፡

ለፓርቲዎች በተወሰኑ ርዕዮተ ዓለሞች ዙሪያ አለመሰባሰብ የገዢው ፓርቲ ስውር እጆች ትልቁ ችግር ሆኖ ቆይቷል የሚሉት ፕሮፌሰር መረራ ጉዲና ገዥውን ፓርቲ የሚወክሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከዚህ ቀደም ፓርቲዎችን ለመፈረካከስ የሚዳርጋቸው ችግር እንደማይኖር እየተናገሩ መሆኑ ዕድል የሚሰጥ ነው ይላሉ፡፡

ከዚያም አልፎ ኢህአዴግ ራሱን በአንድ ሀገራዊ ፓርቲ ለማዋቀር መወሰኑ ሌሎችን ፓርቲዎች እንዲሰባሰቡና በጣም ጥቂት ጠንካራ ፓርቲዎች ተመስርተው በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ ለውጥ እንዲመጣ በር ከፋች ይሆናል ተብሎ ይታመናል፡፡ ሌሎች ተፎካካሪ ፓርቲዎችም ፍላጎቱ ካላቸው የዚህ አገራዊ ፓርቲ አካል መሆን እንደሚችሉ ተጠቁሟል፡ ፡ ይሁን እንጅ የፖለቲካ ምሁራን ይህ ሁኔታ ይፈጠራል ብለው አያምኑም፡፡ ሁሉንም ግን በጊዜ ሂደት እናያለን፡፡


# የመቄዶኒያ አባል ይሁኑ!

- 8151 ላይ በነፃ ቴክስት በማድረግ የመቄዶንያ አባል ይሁኑ
- ወደ 8151 በነፃ 1 ብለው ቴክስት ሲያደርጉ በቀን 1 ብር ለመቄዶንያ ይረዳሉ፡፡
- ወደ 8151 በነፃ 2 ብለው ፅፈው ሲልኩ በሳምንት 2 ብር ለመቄዶንያ ይረዳሉ፡፡
- ወደ 8151 በነፃ 3 ብለው ፅፈው ሲልኩ በሳምንት 3 ብር ለመቄዶንያ ይረዳሉ፡፡

አሁኑኑ በሞባይል ስልክዎ በነፃ ወደ 8151 አባል ሆነው ይመዝገቡ፣ 1፣2 ወይም 3ን ብቻ ፅፈው በነፃ ይላኩ፡፡

**የመቄዶንያ አባል ሆነው ከተመዘገቡ በኋላ በ8161 የመቄዶንያን መልዕክቶች እንልካለን፡፡ የ1 ብር እርዳታ እያደረጉ አረጋውያን ከጎዳና እንዲነሱ ለሚያደርጉ ተሳትፎ እጅግ አድርገን እናመሰግናለን፡፡**

ስፖርት በቁም ነገር

# ዮሚፍ ቀጀልቻ እና ሳሙኤል ተፈራ




## ሁለቱ ኮከቦች

ከሰሞኑ ሁለት ኢትዮጵያውያን አትሌቶች በሁለት ሳምንታት ጊዜ ውስጥ አዳዲስ ክብረወሰኖችን በማይጠበቁ ርቀቶች ሰብረዋል፡፡ በኢትዮጵያውያን እጅ ውስጥ የሚገኙ ክብረወሰኖችን ብዛትም 24 አድርሰውታል፡፡ ዮሚፍ ቀጀልቻና ሳሙአል ተፈራ፡፡

## ዮሚፍ ቀጀልቻ

አሜሪካ ቦስተን ውስጥ በተካሄደ የአንድ ማይል (1.6 ኪሎ ሜትር) የቤት ውስጥ ውድድር ከ22 ዓመታት በፊት በሞሮኳዊው አትሌት ሂሻም ኤልግሩዥ ተይዞ የነበረውን ሪከርድ ኢትዮጵያዊው አትሌት ዮሚፍ ቀጀልቻ ሰብሮታል።

ከስድስት ቀናት በፊት እሁድ እለት በተደረገው በዚህ የቤት ውስጥ ውድድር 3፡47፡01 በመግባት ሪከርዱን አሻሽሏል። በዚህ ውድድር ላይ አሜሪካዊው ጆኒ ግሬጎሬክ 3፡49፡98 በመግባት በሁለተኛነት አጠናቋል።

"ሪከርድ መስበር በጣም ደስ ይላል፤ አንድ ሰው የሚሮጠው የሆነ ነገር ለማግኘት ነው" የሚለው አትሌቱ ለሯጭም ከፍተኛ ደረጃ እንደሆነ ይናገራል።

"አንድ አትሌት በህይወቱ የሚያስደስተው ነገር ኦሎምፒክ ማሸነፍና የአለም ሪከርድ መስበር ነው። ስለዚህ በጣም ደስ ብሎኛል" በማለት ለቢቢሲ ገልጿል።

ሪከርድ በመስበሩ የሚያገኘው ገንዘብ ምን ያህል እንደሆነ ከቢቢሲ ለቀረበለት ጥያቄም ከዚህ ቀደም ሪከርድ የሚሰብር የሚያገኘውን ያህል እንደሆነ ተናግሯል። በኤልግሩዥ ተይዞ የነበረውን ሬከርድ በአንድ ደቂቃ በአርባ አራት ሰከንዶች ያሻሻለው ዮሚፍ በሶስተኛው ሙከራ ሪከርድ መስበር እንደቻለም ተዘግቧል።

የ21 አመቱ ዮሚፍ ከሶስት ሳምንታት በፊት ኒውዮርክ ውስጥ በተመሳሳይ ርቀት ውድድር ያደረገ ሲሆን፤ በወቅቱም በ0.01 ሰከንድ ዘግይቶ ሪከርዱን ሳይሰብር ቀርቷል። በወቅቱ ስለነበረው ስሜትም አትሌቱ ለቢቢሲ ተናግሯል " ያኔ በጣም ተሰምቶኝ ነበር፤ ውድድሩን ስጨርስ ዝቅ ብየ ቢሆን ኖሮ ሪከርዱን እሰብረው ነበር።" የሚለው አትሌቱ በቀጣይነትም ረጅምና መካከለኛ ርቀት የመሮጥ እቅድ እንዳለው ተናግሯል።

"ትልቁ ሀሳቤ ከቤት ውጭ በአምስት ሺ ሜትር ሪከርድ መስበር ወይም ፈጣን ሰአት




ማስመዝገብ እፈልጋለሁ" ብሏል። ዮሚፍ ያስመዘገበው ሰአት በኢትዮጵያም ውስጥ ፈጣኑ ሲሆን ይህም በአማን ወጤ 3፡48፡60 ተይዞ የነበረውን አሻሽሎታል ማለት ነው፡፡

## ሳሙኤል ተፈራ

የ19 ዓመቱ አትሌት ሳሙኤል ተፈራ ከሶስት ሳምንታት በፊት በበርሚንግሃም እንግሊዝ ተካሂዶ በነበረው የቤት ውስጥ የሩጫ ውድድር የዓለም ክብወሰንን በማሻሻል አሸንፏል።

በ1500 ሜትር የቤት ውስጥ ውድድር በሞሮኳዊው አትሌት ሂሻም ኤልግሩዥ እአአ 1997 ተይዞ የነበረዉን 3፡31፡18 ክብረ ወሰን በ14 ማይክሮ ሰከንዶች በማሻሻል አትሌት ሳሙኤል ተፈራ አሸናፊ መሆን ችሏል።

አትሌቱ የቤት ውስጥ ሩጫን ከዚህ በፊት አሸንፎ ስለማያውቅ የማሸነፍ ግምት አልተሰጠውም ነበር። ይልቁንም ባለፉት ሳምንታት ውድድሮቹን በድል ሲያጠናቅቅ የቆየው ዮሚፍ ቀጄልቻ ከፍተኛ የአሸናፊነት ግምት ተሰጥቶት ነበር። ዮሚፍ በዚህ ውድድር 3፡31፡58 በመግባት በርቀቱ የግሉን ምርጥ ሰዓት ማስመዝገብ ችሏል።

"በጣም ደስተኛ ነኝ፤ ደስታዬ ይሄ ነው ለማለት ይከብደኛል። ወደዚህ ውድድር የገባሁት በግፊት እንጂ የራሴ ሃሳብ ኖሮኝ አይደለም። የፈጣሪ እርዳታ ነው" በማለት ሳሙኤል ለቢቢሲ በወቅቱ አስተያየቱን ተናግሯል።

ሳሙኤል በውድድሩ ላይ እንዴት እንደተሳተፈ ሲያስረዳ "የዓለም ሪከርድን አሻሽላለሁ ብዬ አይደለም ወደ ስፍራው ያቀናሁት። ኔዘርላንድ እና ፈረንሳይ ለነበሩኝ ውድድሮች ላይ ለመሳተፍ ነው ወደ አውሮፓ ያቀናሁት። እኔ ሃሳቤ የነበረው የኔዘርላንድ እና ፈረንሳይ ውድድር ተሳትፌ ወደ ኢትዮጵያ መመለስ ነበር። ነገር ግን እንዳጋጣሚ ሆኖ ይህ ውድድርም አውሮፓ እያለሁኝ የሚካሄድ ስለነበረ በጣም በተጣበበ ሁኔታ ተወዳድሬ ነው ማሸነፍ የቻልኩት" ብሏል።

> “
>
> **ጨዋታው ወደ ፍጹም ቅጣት ምት ሲያመራ፣ አሰልጣኙ የፍጹም ቅጣት ምት ኳሶችን የማዳን ብቃቱን በ2016 ማንችስተር ሲቲ ከሊቨርፑል ጋር ባደረጉት ጨዋታ ባዳናቸው ሦስት ኳሶች ብቃቱን ያስመሰከረውን የቀድሞው የማንቼስተር ሲቲ ግብ ጠባቂ ዊሊ ካባሌሮን ለማስገባት ፈለጉ፡፡**

ሳሙኤል ያሻሻለው ሪከርድ እሱ ከመወለዱ በፊት የተያዘ ነበር። አትሌቱ ገና 19 ዓመት ወጣት ሲሆን ይህ ውድድር በማሸነፉ 3ሺህ ዶላር እንዲሁም ሪከርድ በመስበሩ 30ሺህ ዶላር ተሸላሚ ለመሆን በቅቷል። ከዚህ ቀደም ምንም አይነት የዓለም ሪከርዶችን አሻሽሎ እንደማያውቅ የሚያስረዳው ሳሙኤል ለመጀመሪያ ጊዜ ያሻሻለው ሪከርድ ለሌላ ስኬት እንደሚያነሳሳው እና ወደፊትም ጠንክሮ እንዲሰራ ብርታት እንደሚሆነው ይናገራል።

በዚህ ውድድር በሁለተኛ ደረጃ ያጠናቀቀው ዮሚፍ፤ ከሳምንት በፊት በኒው ዮርክ የአንድ ማይል ሩጫ ተይዞ የነበረውን ክብረ ወሰን በአንድ ማይክሮ ሰክንድ ዘግይቶ በመግባቱ ሳያሻሽል ቀርቷል። በዚህም ምክንያት ይህን ውድድር ያሸንፋል ተብሎ ከፍተኛ ግምት ተሰጥቶት የነበረው ዮሚፍ ቀጄልቻ ነበር። የሳሙኤልም ሃሳብ ይሄ ነበር።

"ለአንድ ማይክሮ ሰከንድ ሳያሻሽል መቅረቱ በጣም አሳዝኖኝ ነበር። በዚህም ውድድር ዮሚፍ ያሸንፋል የሚል ግምት ነበረኝ። እኔም የዮሚፍ ጥሩ ተፎካካሪ እንደምሆን እራሴን አሳምኜ ነበር የገባሁት" ብሎ ነበር ሳሙኤል።

ምዕራብ ሸዋ ሚዳ ቀኝ ወረዳ የተወለደው ሳሙኤል በ2007 ዓ.ም የ10 ኛ ክፍል ትምህርቱን በማቋረጥ ነው ፊቱን ወደ አትሌቲክስ ስፖርት ያዞረው፡፡ እናም በ2008 የኦሮሚያ እንስሳትና ደን ጥበቃ ክለብን ተቀላቀሎ በተለያዩ ውድድሮች መሳተፍ ጀመረ፡፡ በ2009 ኢትጵያን ወክሎ የአለም ሻምፒዮና ላይ ቢሳተፍም ውጤታማ ሳይሆን ቀርቷል፡፡ በ2010 የአለም የቤት ዉስጥ ሩጫ ውድድር ግን በ1500 ሜትር የወርቅ ተሸላሚ ሆኗል፡፡



# አዲስ መፅሐፍ በገበያ ላይ!

## 2000 የጠቅላላ እውቀት ጥያቄና መልስ መፅሐፍ


መፅሐፉን ከሚከተሉት አከፋፋዮች ማግኘት ይቻላል!

- አይናለም መፅሀፍ መደብር ብሔራዊ ቴአትር ጀርባ
- ጃፋር መፅሀፍ መደብር ለገሀር-
- ከድር መፅሀፍ መደብር ለገሀር
- ቃልኪዳን መፅሀፍ መደብር አራት ኪሎ
- መኮንን መፅሀፍ መደብር ጊዮርጊስ
- ጌታቸው መፅሐፍ መደብር ጊዮርጊስ
- ፍሬው መፅሐፍ መደብር 5 ኪሎ

- ታደሰ መፅሀፍ መደብር አውቶብስ ተራ
- ዋሸራ መፅሀፍ መደብር አውቶብስ ተራ
- ዮሐንስ መፅሀፍ አውቶብስ ተራ
- ከድር መሐመድ መፅሐፍ መደብር

-- በሁሉም የሚጋ ማከፋፈያ ቅርንጫፎች ይገኛል።

6ኛ ዕትም




6ኛ ዕትም

- መፅሐፉን ገዝተው ከራስዎ ጋር ይወዳደሩ!




ለበለጠ መረጃ 0911-232015/0115-507410 ይደውሉ!

## ብሔራዊ እርቅ.....

ከገጽ 17 የዞረ

የተሞላው የግል ውሳኔ ላይ ሊደርሱ ይገባል።

❖ የእርቀሰላም ጉዳይ የስልጣን ማግበስበስ ወይም የፖለቲካ ታዋቂነትን ለማግኘት የሚደረግ ስትራተጂ መሆን የለበትም። ለሀገራችን እጅግ ጠቃሚና ወሳኝ ተግባር መሆኑን በመገንዘብ ከግልና ከድርጅት ጥቅም በላይ የሀገርን ጥቅም ለማስጠበቅ መወሰን ከእያንዳንዱ የኮሚሽኑ አባል የሚጠበቅ ተግባር ነው። የኔ በኮሚሽኑ ውስጥ መቀጠል በኮሚሽኑ ታአማኒነትና፣ ገለልተኛነት፣ እንዲሁም በተጎጂዎች ላይ የሚኖረው ተጽእኖ ምንድን ነው ብሎ ራስን መጠየቅ ጊዜው የሚጠይቀው ተግባር ነው።

❖ ጋዜጠኞች የሲቪክ ማህበረሰቡ አባላትና ሌሎችም ባለድርሻዎች ሁኔታውን በጥልቀት መመርመር አስፈላጊ ሲሆንም በመተቸት ማሻሻያ ሀሳቦችን በማቅረብና ተመራጮችንም ተጠያቂ በማድረግ ሁኔታው ባግባቡ ሊጠናከርና ጠርቶ ሊጓዝ የሚችልበትን ሁኔታ ሊያግዙ ይገባል።

❖ የለውጥ ሀይሉ (መንግስት) በሚያካሂደው መልካም ተግባር መሞገስ ሲገባው ማሞገስና ማበረታታት ስህተት ሲታይ ደግሞ አግባብ ያለው ወቀሳና የማስተካከያ ሀሳብ ማቅረብ ተገቢም የዜግነትና ሙያዊ ሀላፊነትም ነው።

❖ የፖለቲካ ድረጅቶች በእንደዚህ አይነት ቁልፍ ጥያቄ ላይ ዝምታን መምረጣቸው ሀላፊነትን አለመወጣት ብቻ ሳይሆን እጅግ አሳዛኝ ተግባርም ነው።የዚህ አይነት ዝምታ ለሀገራችን ዴሞክራሲ ግንባታ ጉዳት እንጂ ጠቀሜታ የለውም። ይህ የፍራቻ ባህል፣ በአድርባይነትና በአክራሪ ተቃዋሚነት ጫፍ የተንጠለጠለ አሰራር ሊቀየር ይገባዋል።

❖ መንግስት ሳይዘገይ አስፈላጊውን ማስተካከያዎችን (የማሻሻያ አዋጅን ጨምሮ)፡ በማድረግ የኮሚሽኑን ታማኒነት ከፍ እንዲል ጥረት ማድረግ ይጠበቅበታል።' በኮሚሽኑ ስራ ውስጥ ጣልቃ አልገባም በሚል ሰበብ የተበላሸ ሂደት እንዲቀጥል ማድረግ እጅግ አሳዛኝ ሲሆን አሁንም ሀገራችን ሌላ የግጭት አዙሪትን የምትሰብርበትን እድል እንዲያመልጣት ሊያደርግ ይችላልና የእርምት እርምጃ ባስቸኳይ መውሰድ ተገቢ ነው።

❖ በኔ አመለካከት የፖለቲካ ድርጅት መሪዎች ከኮሚሽን አባልነት ወጥተው ኮሚሽኑ በሚፈልግበት ጊዜ የአማካሪነት ሚና የሚጫወት አካል ሆነው ቢቀጥሉ የተሻለ ውጤትን ሊያስገኙ ይችላሉ።

❖ የመንግስት ባለስልጣኖች በተለይም በቅርብ ጊዜ በከፍተኛ ሀላፊነት ላይ የነበሩ ከኮሚሽኑ መወገድ አለባቸው። የነርሱ መቀጠል ኮሚሽኑን ተልእኮ ገና ከመጀመሪያው የከሸፈ ያደርገዋል።

❖ በኮሚሽኑ ውስጥ የሚሳተፉ ሁሉ ተልእኮው የሚጠይቀው የጤና ብቃት እንዳላቸው ማረጋገጥ ተገቢ ይሆናል።

❖ ባጠቃላይ የ እርቀሰላምን (ብሄራዊ መግባባት) አይነት ክብደት ያላቸው ሀገራዊ ጉዳዮች እንደውጤታቸው ሁሉ አካሄዳቸውም እጅግ ታላቅ ጠቀሜታ ስላላቸው ገና ከጅምሩ በከፍተኛ ጥንቃቄ ሊያዙ ይገባል።

It is in our hand to create a better world for all who live in it.Mandela

**ከአዘጋጁ:- ይህንን ጽሑፍ በካናዳ ነዋሪ የሆኑት አቶ አክሊሉ የሚመለከታቸው አካላት እንዲወያዩበት በሀገር ውስጥ መገናኛ ብዙሃን እንዲቀርብ ለቁም ነገር መፅሔት የላኩት ነው፡፡**

## ጠቅላይ ሚ/ሩ

ከገጽ 28 የዞረ

ያገኘውን ነገር ሁሉ አተረማመሰ፡ ፡ ንጉሡ ከዚህ ድብልቅልቅ የወጣው በመከራ ነው፡፡ በጣም ከመናደዱ የተነሳም ቤተ መንግሥቱ እንደደረሰ ስለ አየር ሁኔታው የተሳሳተ መረጃ የሰጡትን ሁሉ አባረረ፡፡ ከነዚህም መሀል ዋናውን ኮከብ ቆጣሪ፣ ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ በጠቅላላ ሚኒስትሮችና ከአየር ትንበያ ጋር ግንኙነት ያላቸውን የቤተመንግሥት ባለስልጣናትም ነበሩበት፡፡

ስለ መጥፎው አየር ሁኔታው ተንብዮ እውነት የሆነለትን መንደረተኛ ንጉሡ አስጠራው፡፡ አህያው ጭራ ላይ ታስሮ ረጅም መንገድ ስለተጎተተ ሙሉ ለሙሉ ተዳክሟል፡፡ ንጉሡም ጠቅላይ ሚኒስትር አድርጎ ሾመው፡፡

«ከአሁን ጀምሮ የአገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስትር፣ አድርጌ ሾሜሀለሁ፡ ፡»

መንደረተኛው ለጥቂት ቀናት የአገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስትር ሆኖ እንደሠራ፣ ንጉሡ ሀሳቡን ሰብስቦ ወደ ቤተ መንግሥቱ አስጠራው፡፡

«እስቲ ንገረኝ፣ ያን ዕለት እንደሚዘንብ እንዴት አወቅህ?»

«ግርማዊነትዎ ሆይ፣» ሲል ጠቅላይ ሚኒስትሩ መለሰ፡፡ «የአየር ሁኔታውን በትክክል ለመተንበይ የሚረዱኝን የአህያዬን ጆሮዎች እከታተላለሁ። የሚዘንብ ከሆነ ቀጥ ያሉ የአህያዬ ጆሮዎች ያዘነብላሉ፡፡ ያን ዕለት ጆሮዎቹን በዚህ አይነት አቋም አየኋቸውና እንደሚዘንብ ነገርኩዎት፡፡

«ምን አይነት የማልረባ ሰው ነኝ!» አለ ንጉሡ፡፡ «የአየር ሁኔታውን በትክክል የተነበየው መንደረተኛው ሳይሆን አህያው ነው፡፡ አህያው የሚያውቀውን ያህል እንኳን የማያውቁ ሚኒስትሮችና ጠቅላይ ሚኒስትር አሉ፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትርነቱን ለመንደረተኛው በመስጠቴ አህያው የአገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስትር የመሆን መብቱን ነፍጌዋለሁ?»

ንጉሡ ጊዜ ሳያጠፋ መንደረተኛውን ሻረና አህያውን አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትር አድርጎ ሾመው። ከዛ ጊዜ ጀምሮ አየሩ ጥሩ በሚሆንበት ጊዜ አህያው በደስታ ያናፋል፣ ንጉሡም መልእክቱ ይገባዋል፡፡ አውሎ ነፋስ እየመጣ ከሆነም ጠቅላይ ሚኒስትሩ ጭራውን ቀጥ ያደርጋል፣ የሚዘንብ ከሆነ ደግሞ ጆሮዎቹ ወዲያውኑ ያዘነብላሉ፡፡

ከዛ በኋላ ንጉሡ በደስታ ኖረ፡፡ የአዲሱን ጠቅላይ ሚኒስትር ምክር መቼም ቢሆን፤ በተለይ አደን መውጣት በፈለገበት ጊዜ ችላ ብሎት አያውቅም፡፡

ምንጭ:- («ራሴን አጠፋሁ እና ሌሎችም» ከሚለው መድብል የተወሰደ) ድርሰት:- አዚዝ ኔሲን ትርጉም:- ኤፍሬም እንዳለ


# ሜሪ ጆይ የልማት ማህበር

የእርስዎ ማንኛውም ድጋፍ (በገንዘብ፣ በቁሳቁስ፣ በአልባሳት...) የህፃናት ድጋፍ(ስፖንሰር ሺፕ) ለአንድ ህፃን 300 ብር በወር፣ የአረጋውያን ድጋፍ (ስፖንሰር ሺፕ) ለአንድ አረጋዊ 300 ብር በወር፣ የድርጅቱ አባል መሆን (ፕላቲኒየም፣ ወርቅ፣ የብር...) ቀጣዩን ትውልድ በመንከባከብና በማስተማር እንዲሁም አረጋዊያን ቀሪ ዘመናቸውን በደስታ ያሳልፉ ዘንድ እያንዳንዳችን ሃላፊነታችንን እንወጣ! በጋራ በምንደግፋቸው ህፃናትና አረጋዊያን ህይወት ላይ ለውጥ እናምጣ!

ማህበሩ አድራሻ:- መገናኛ ከዲያስፖራ አደባባይ ወደ ቶፕ ቪው (የካ ተራራ ት/ቤት) መውጫ 50 ሜትር ገባ ብሎ

ለበለጠ መረጃ ስልክ 0118-96-63-21/22/23 ሞባይል 0911 20 85 18

# አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትር

/በኤፍሬም እንዳለ/



‹‹አድማሱ ሐምራዊ፡ አየሩ ግሩም ነው፡፡ ፈጣሪ ሁልጊዜም የግርማዊነትዎ ርህሩህ ጥላ ራሳችንን እንዲከላከልልን ያድርግልን፡፡

ከዕለታት አንድ ቀን ከዚህ ዓለም ሀገራት በአንዱ አንድ ንጉሥ ነበር፡፡ እንደማናቸውም ንጉሦች ይህኛውም ንጉሥ የራሱ ሙዚቀኞች ዳንሰኞች፣ ውሽሞች፣ ባሮች፣ ጫማ ሳሚዎችና የመሳሰሉት ነበሩት፡፡ እንደ መክፈቻ ሥነ ሥርዓቶች ላይ መሳተፍ፣ ወታደራዊ ሰልፍ መመልከት፣ ከሌሎች የተጻፉ ንግግሮችን ማንበብና ጉብኝት ማድረግ ከመሳሰሉ በርካታ ኦፊሴላዊ ተግባራቱ የተረፈ ጊዜ ሲያገኝ አደን ይሄዳል፡፡

ሆኖም የአየር እርጥበት ምቾት የማይሰጠው በመሆኑ የሚገጥመውን የአየር ሁኔታ በደንብ ሳያረጋግጥ መቼም ቢሆን አደን አይወጣም። ዋናውን ኮከብ ቆጣሪውን ያስጠራና ስለ አየር ሁኔታው ትንበያ ከእሱ ይሰማል፡፡

ዋናው ኮከብ ቆጣሪም ዘወትር «በእርሶ ምክንያት የአገራችን አየር ሁኔታ ሁልጊዜም ብሩህና በፀሐይ ብርሃን የተሞላ ለሆኑት ሞገስ ለተሞሉት ግርማዊነትዎ ረጅም ዕድሜ፡፡ የአየር ሁኔታው ግርማዊነትዎ እንደሚፈልጉት ጥሩ ይሆናል፡፡»

ንጉሡ እንደ ሁሉም ነገሥታት ተጠራጣሪ በመሆኑ ጠቅላይ ሚኒስትሩን ጠርቶ የአየር ሁኔታው ምን እንደሚሆን ይጠይቀዋል። የጀሮው ፀጉር ሳይቀር የሸበተውና ከሆዱ በታች የተንጠለጠለ ጢም ያለው ኃያሉ ጠቅላይ ሚኒስቴር ጢሙ የንጉሡን እግር እስኪነካ ድረስ ይንበረከክና፤ «በግርማዊነትዎ ሩህሩህ ጥላ ስር በአገር ውስጥም ሆነ ከአገር ውጪ ያለው ፖለቲካዊ ሆነ ፖለቲካዊ ያልሆነ የአየር ሁኔታ በፈጣሪ ፍቃድ በጣም ጥሩ ይሆናል፡፡”

ተጠራጣሪው ንጉሥ ከዛም እያንዳንዱን ሚኒስትር በየተራ ስለ አየር ሁኔታ ይጠይቅና ከሞላ ጎደል እንዲህ የሚል ምላሽ ያገኛል፡-

«አድማሱ ሐምራዊ፡ አየሩ ግሩም ነው። ፈጣሪ ሁልጊዜም የግርማዊነትዎ ርህሩህ ጥላ ራሳችንን እንዲከላከልልን ያድርግልን። ግርማዊነትዎ እስካሉ ድረስ የአየሩ ሁኔታ መልካም እንጂ ሌላ የመሆን ዕድል የለውም፡፡»

በመጨረሻም በራስ መተማመኑና በገደብ የለሽ ስልጣኑ በመመካትና የባለሙያዎቹን የፖለቲካ መሪዎች ምክር በመንተራስ ንጉሡ በልዩ ሁኔታ የተባዙ እንስሳት ወዳሉበት ልዩ ጫካ ይሄዳል፡፡ የአደን ቁሳቁሶቹ በተመረጡ ሰዎች ትከሻዎች ላይ ይጫናሉ። ሁሉም ሕይወታቸውን ለንጉሡ ለመሰዋት ፈቃደኛ በሆኑ ከፊት ፖሊሶችና ዘቦች፣ ከጎን ጎን የጦር ኃይል ክፍሎች በተጨማሪም በመንገዱ የተበታተኑ በርካታ በጎ ፈቃደኞች፣ መሀል ላይ ንጉሡ፡፡ በተጨማሪም በእንደዚህ አይነት ንጉሡን የሚያጅቡ በርካታ የሲቪልና ወታደራዊ ባለስልጣናት አሉ፡፡

ሁኔታዎች በመልካም ሁኔታ እየሄዱ ነበር፡፡ አንድ ቀን ንጉሱ በተከታዩ ቀን አደን ለመሄድ ይወስናል።

ዋናውን ኮከብ ቆጣሪ፣ ጠቅላይ ሚኒስትሩን፣ እያንዳንዱን የካቢኔ ሚኒስትር፤ የኃይማኖት መሪውን፣ ዋናው ፀሀፊን፣ የውሽሞች ሀላፊን፣ የቤተ መንግሥቱ የእልፍኝ አስከልካዩን እያለ በደረጃ ተዋረድ የአየር ሁኔታው እንዴት እንደሚሆን ጠየቀ፡፡ ከሁሉም የተለመደውን መልስ በማግኘቱ ወደ አደኑ አቀና፡፡

የንጉሡ አጀብ የሚያልፍበት መንገድ ሁሉ በደህንነት ሰዎች ተበጥሮ የተፈተሸ ቢሆንምና ማንም ተራ ሰው የንጉሡ አጀብ በሚያልፍበት ዝር እንዳይል ቢደረግም አንድ መንደረተኛና አህያው እንደምንም በመንገዱ ላይ አንድ ዛፍ ስር ተጠልለው መቆየት ችለው ነበር፡፡ ንጉሡ በህይወቱ ሙሉ አንድም መንደረተኛ አይቶ አያውቅም፡፡ በቡቱቶ የተጠቀለለና ባዶ እግሩን የሆነ ፍጡር ሲያይ ምን እንደሆነ ተገረመ፡፡ ህይወት ከሌለው ግዑዝ ነገር ሌላ ይሆናል ብሎ ሊያስብ አይችልም ነበር፡፡ ለማወቅ በመጓጓት ወደ መንደርተኛው ተጠጋ፡፡ ፊት ለፊቱ ያለው እንግዳ የሆነ ፍጡር ህይወት ያለው መሆኑን ሲገነዘብ ንጉሡ በመገረም፤ «አንተ ማነህ? ሰብአዊ ፍጡር ወይስ መንፈስ?» ሲል ጠየቀው።

«መንፈስ አይደለሁም» ሲል መንደርተኛው መለሰ፡፡ «ልክ እንደ እርሶ የአዳም ልጅ ነኝ፡፡»

ንጉሡ ይህን ስርአት የለሽ መልስ ሲሰማ ተናደደ። «ምን አይነት ብልግና ነው! እንዲህ አይነት ነገር ከእኔ ዘር ሊመጣ አይችልም። ቶሎ በሉና አንገቱን ቀንጥሱት፣» ሲል አዘዘ። ጎራዴው መንደረተኛው አንገት ላይ ከማረፉ በፊት ንጉሡ፣ «ቆይ!» ብሎ ጮኸ፡፡ መንደረተኛውንም አናገረው፡፡

«አንተ ቃላቶችህ የሰውን ልጅ ንግግር የሚመስሉ ልዩ ፍጡር፤ አንድ ነገር ልጠይቅህ እፈልጋለሁ፡፡ መልሱን ከሰጠኸኝ ትተርፋለህ፡፡ በዛሬው ቀን የአየር ሁኔታው ምን ይመስላል?»

«ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ኃይለኛ ነፋስ መንፈስ ይጀምራል፡፡ ከዛ ዶፉን ይለቀቀዋል” ሲል መንደረተኛው መለሰ፡፡

ንጉሡ ከመንደረተኛው አንደበት እነኚህን ቃላት ሲሰማ ብው አለ፡፡ «አንተ ከሀዲ! እኔ አደን ለመውጣት ከወሰንኩ በምንም አይነት አየሩ መጥፎ ሊሆን እንደማይችል አታውቅም? እኔ አደን ወጥቼ እንዴት ብሎ ነው የሚዘንበው? ይህን ፍጡር ፍጠኑና ከበቅሎዋ ጭራ ጋር እሰሩልኝ!»

መንደረተኛውን ከራሱ አህያ ጭራ ጋር አሠሩትና አህያው ደግሞ ከበቅሎይቱ ጋር ታሠረ፡፡ የአንዲት ጦር ርዝመት ያህል እርቀት ሳይጓዙም ሰማዩ ጠቆረ። ከባድ የጠቆሩ ደመናዎች ይጥመለመሉ ጀመር፡፡ የንጉሡም አጀብ በመብረቅ ነጎድጓድ ተተራመሰ። ከዛም ኃይለኛ ዶፍ በመውረዱ አካባቢው በጎርፍ ተጥለቀለቀ፡፡ ከባድ ነፋስም እያፏጨ

ወደገጽ 27 ዞሯል

# የሜሲ…

ከገጽ 29 የዞረ